“ራስህን አስለምድ”

“እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምዶች”

በመጋቢ በድሉ ይርጋ (ዶ/ር)

"ራስህን አስለምድ"

ጸሐፊው እና አሳታሚው መጋቢ በድሉ ይርጋ (ዶ/ር)

የቅጂው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::

የመጀመሪያው ዕትም በወርኀ የካቲት 2009 ዓ.ም ታተመ::

በግልጽ ካልተቀመጠ በስተቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትም የተወሰዱ ናቸው::

ተንጋደው የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወይም ቃላት ለአጽንዖት ያህል ብቻ ታስበው የተደረጉ ናቸው::

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ለማሳተም ወይም በማናቸውም የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ለማባዛት የጸሐፊውን በጽሑፍ የተሰጠ ይሁንታን ማግኘት ይጠይቃል::

አስተያየት ወይም ጥያቄ ቢኖርዎ በሚከተለው የኢ-ሜይል አድራሻ ያገኙናል:-
bediluy@gmail.com

ዳላስ፣ ቴክሳስ፣ አሜሪካ
የካቲት 2009 ዓ.ም

ማውጫ

ምስጋና I
አስተያየት III
መግቢያ V

ምዕራፍ አንድ
እግዚአብሔርን ምሰሉ! 1

ምዕራፍ ሁለት
ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ! 12

ምዕራፍ ሦስት
ለብቻችሁ በፀጥታ በእግዚአብሔር ፊት አረፉ! 28

ምዕራፍ አራት
ኦሮን ቀሰል አድርጋችሁ ኑሩት! (አትጠላለፉ) 45

ምዕራፍ አምስት
ለገሌጋይ ሁኑ! 64

ምዕራፍ ስድስት
ራሳችሁን ለመሥዋዕትነት አዘጋጁ! 79

ምዕራፍ ሰባት
ወዳጅነትን አጥብቁ! 96

ምዕራፍ ስምንት
ወንጌልን አብስሩ! 113

ምዕራፍ ዘጠኝ
ጸሎት ሕይወታችሁ ይሁን! 129

ምዕራፍ አስር

ተማሩ! (የሚማር ልብ ይኑራችሁ) 145

ምዕራፍ አስራ አንድ

ደስ ይበላችሁ! 163

ማሳረጊያ 179

ምስጋና

እስቀድሜ በወንጌል የሚገኘውን የድነት ተስፋ ምን እንደሆን እንድሰማ፣ እንድረዳውና እንዳምን የሚያስፈልገኝን ጸጋ ሁሉ የሰጠኝን እግዚአብሔር አምላኬና መድኃኒቴን እመሠግናለሁ። ደግሞም የዳንኩበትን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለሌሎች እንዲካፈል ጸጋውን እና ዕዳሎቱን (ጥሪውን) የሰጠኝን ጌታ እከብረዋለሁ። ክብርና ሞገስ፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ይሁን!!!

የመጽሐፉ ይዘት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በተከታታይ ትምህርት ሆኖ ረዘመ እሁን በማገለግልበት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን የእሁድ ጠዋት መድረኮች ነበር። በዚያን ወቅት መልዕክቱ እንደሚገባ ለስሚ እንዲቀርብ በጸሎት የደገፉኝን፣ እንደ ዛሬም በጽሁፍ ለአንባቢያን እንዲቀርብ ያለማቋረጥ ያበረታቱኝና የውተውቱኝ ውድ የዳላስ ቤተ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች እንዲሁም መሪዎችና አገልጋዮች በሙሉ ከአንጀቴ ጌታ አብልጠና አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ። ያለ እናንተ የጸሎት ድጋፍ የሆነው ባልሆነ ነበር። እናንተንም ዘራችሁንም ለክብሩ ያባዛልህ።

እንብበው አበረታች አስተያየታቸውን የለገሱኝን ፓስተር ዶክተር ተስፋ ሠርቶህ፣ ዶክተር ሺፈራው ወልደ ሚካኤል፣ ፓስተር እንዳልክ ሳህሌ፣ ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን፣ ወንድም ሚኪያስ በላይ እና ወንድም ዘላለም እበበ አመሰግናችኋለሁ። የሽፋኑን ዲዛይን ያበጀልኝን ወንድሜና እብሮ እገልጋይ የሆነው ዘማሪ ዳንኤል አምደ ሚካኤል ጌታ ይባርከህ!! ከስብከት ቃል ወደ ጽሁፍ የመለወጡን አድካሚ ሥራና እርታኒነቱን የተወጣው ናዝሬት ኢትዮጵያ የሚገኘውን ወንድሜ ሰሎሞን እስፋ ባዘኑን ከላይ ይጨምርብህ እላለሁ። ደጋግሞ ረቂቁን እንብቦ እርማቱን በጊዜው ያቀረበልኝን የዳላሱ ወንድም ካሣ ወርቅነህን ከነቤተሰቡ ጌታ እጅጉን ይባርካቸው አላለሁ።

በየዕለቱ ከጌታ ጋር ለምኖረው ኑሮና የእገልግሎት ጥሪ ምላሼ ያልተቆጠበ ድጋፉ የምትሰጠኝ የ31 ዓመታት የትዳር ጓደኛዬና ወዳጄን አልማዝ ደሳለኝ፣ ልጆቻችን አሰሃ እና መጋቢ ዳዊት ይርዳው፣ ሌዊ እና እዲስ እንዲሁም ቀዳሚ የልጅ ልጃችን ሐናን ሁሉ በምህረቱ ባለጠጋ የሆነው ጌታ በእውነተኛው መንፈሳዊነት ልምምዶች ይባርከን!!!

በየአሁዱ ከምስባክ የተላሰፉትን ስብከቶችና ተከታታይ ትምህርቶች a ጽሁፍ በመለወጥ ለአንባቢያን እንድትመች ሆና ይህች ጽሁፍ በርዕሰ ጉ "እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምዶች" ወይም "የእውነተኛ መንፈሳዊነት ልምምድ: ሁሉንም ነጥቦች አካትታለች እልልም። ነገር ግን በአብዛኛው አስፈላጊና አማ ጎብረተሰብ አውቆ ቢለማመዳቸው ውጤቱ ለጌታ ክብር፣ ለሰው ጥቅም እና ለእካ መታነጽ ይሆናል ያልኳቸውን ብቻ ነው ያቀርብኩት። በርዕሰ ጉዳዩ ይበልጥ ጥና ያደረጉና የቃሉን አብርሆት የታደሉ ሊጨምሩበት ይችላሉ። ጸሎቴም ነው። እንግዳ በስብከት ብቻ ተወስኖ ከሚቀር እነሆ ጽሁፉ። በመጨረሻም ማናቸውንም ዓይነ የአንባቢያን ገንቢ አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ መሆኔን በአክብሮት ለመግለ እወዳለሁ።

አስተያየት

ወንድማችን ፓስተር ዶ/ር በድሉ ይርጋ ለረዥም ጊዜ ከአጠራቀመው ልምምዱ እግዚአብሔርን መምሰል እንዴት እንድምንችል የሚያሳዩንን ትምህርቶችን ያዘለቸውን ይህችን መጽሐፍ አቅርቦልናል። "ራስህን አስለምድ" የሚል ርዕስ ይዛ የተረበቸውን ይህችን መጽሐፍ የሚያነቧት ሁሉ ጠቃሚ ትምህርት እንዲሚያገኙባት አምነት ነው።

ፓስተር ዶ/ር ተስፋ ወርቅነህ

ዶክተር በድሉ "እግዚአብሔርን መምስል" በሚለው አዲስ መጽሐፉ በእግዚአብሔር ሥም የተጠራው ሕዝብ በግል፣ በቤተሰብ፣ በሥራው እንደዚሁም በእገልግሎት ሕይወቱ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ ልንሆነው፣ ልናሳየውና፣ ልንታወቅባቸው የሚገቡንን ዋና ዋና መለኪያዎች ገልጦልናል። መጽሐፉ እግዚአብሔርን መምስል ለእያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ የተከፈተ በር፣ የተሰጠ እድል፣ እንደዚሁም ከእያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር እምላክ በጉጉት የሚጠብቀው እንደሆነ ከመጠበስሩም በላይ ሊደረስበት የሚችል ግብ መሆኑንም ያሳያል። ወደ እግዚአብሔር መምስል የሚያደርሱንና እኛ ልንወስዳቸው የሚገቡን ርምጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በተሳለ ቋንቋ ቀርበዋል። በተጨማሪም የደራሲውን የግልና የቤተሰብ እንደዚሁም የእገልግሎት ገጠመኞች ያካተቱ ምሳሌዎች በአብዛኛቹ የመጽሐፉ ምዕራፎች መጠናቸው ለመጽሐፉ ውበትና ትምህርት ሰጭነት ጉልበት ሆነውታል። ይህ መጽሐፍ ሁላችን በግል፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያንና በሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶቸም ብንጠቀምበት እጅግ የሚያስፈልግ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ፖስተር ዶክተር በድሉ ለእግዚአብሔር መንጋ በዚህ መልክ ስለሚሰጠው አገልግሎት እግዚአብሔር ይባርከህ ማለት እወዳለሁ።

ዶክተር ሽፈራው ወልደ ሚካኤል

"እግዚአብሔርን መምሰል" የተሰኘው የመጋቢ በድሉ ይርጋ (ዶ/ር) መጽሐፍ አንደ ስብከት፣ አንደ ትምህርት፣ አንደ ቅርብ ወዳጅ ምክር፣ አንደ ቤተ ክርስቲያን ተግሳጽ፣ ከሁሉም በላይ አንደ እግዚአብሔር ቃል እውነት ልብን ሠርሥሮ የሚገባ መልዕክት የታጨቀበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን "እግዚአብሔርን መምሰል" ሌላ ትርጉም በተሰጠበትና የሰውን ልጅ ከፈጣሪው በአኩያነት ሊያንጠራራው በጀመረበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን አርሱን የመምሰልን ምስጢር ከዚህ መጽሐፍ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል።

ሚከያስ በላይ
የሕንጸት ክርስቲያናዊ ማህበር ዳይሬክተር

አግዚአብሔርን መምሰል አለቀድመን የተፈጠርንበት፣ በኋላም የዳንበት፣ አሁንም ጌታን የምንከተልበትና ወደፊትም የከብሩን መገለጥ የምንጠባበቅበት አንኳር የክርስትና ርዕሰ ጉዳይ ነው። ወዳጄ መጋቢ በድሉ ታንቁ ይርጋ ከዚህ ውቅያኖስ አከል ርዕስ በመጨለፍ አግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ ላይ አተኩሮ ለነፍስ የሚሆን የንባብ ማዕድ አነሆ ብሎናልና በማንበብ ከበረከቱ እንቋደስ።

ያሬድ ጥላሁን (ወንጌላዊ)
ጎልደን አይል አገልግሎት

አግዚአብሔርን መምሰል ግዴታ ነው። የሁሉ ክርስቲያን ጥሪው ነውና መንገዱም ሂደት ነው፤ በአንድ ጀንበር ሊያልቅምና። አሁንማ ገብቶናል ግን እንዴት? ለምንል ለዎች መጋቢ በድሉ ዋና ዋና የሆኑትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገዶችን በዚህ መጽሐፉ ያሳየናል። ያለንበት ዘመን መርህ ጠል የሆነ ነፋስ አየሩን የሞላበት ቢሆንም እግዚአብሔርን ለመምሰል ለጨከኑና "የመንገድ ያለህ" ለሚሉ ግን መሠረታዊ የሆኑ ቁልፎችን አነሆ፤ አግዚአብሔርን መምሰል እርሱ ራሱን ከማወቅ ይጀምራልና የሚቀጥለውን ከመጽሐፉ ያንብቡ፤ ለጊዜውና ለሁሉም ሰው የሚሆን መልዕክት ይዘህ አንደገና በዚህ መጽሐፍ ስላመጣህ ወንድሜ በድሉ አግዚአብሔር ይባርከህ! ሁላችንም አንብበን አንጠቀም ምክሬ ነው።

ዘላለም አበበ
የቀድሞ ኢቫሱ ዋና ጸሐፊ እና በጎርደን ኮንዌል ቴዎሎጂካል ሴሚናሪ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ

መግቢያ

የአግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱሳችን በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እጅግ በርካታ ትዕዛዛዊ ወይም የሰውን ተግባራዊ ምላሽ የሚሹ ቃላት፣ ሐረጎች እና ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ትዕዛዛት ወይም ተግባራዊ ሐሳቦች የረቀቀ ትንታኔ የማያሻቸው እንዲሁ በእንግርቡ እንኳ እንበበን ልንረዳቸው፤ አለፍ ሲልም የሦኑተንብራቸው ሆነው የምናገኛቸው ናቸው። ለዚህ "አትግደል"፣ "አትስረቅ"፣ "በሐሰት አትመስክር" የሚሉት ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

ከዚህ ከፍ ብለን እንዲሁ ደግሞ "ኑና አንዋቀስ ይላል አግዚአብሔር" ሥሚለውን ጥቅስ ከትንቢተ ኢሳይያስ 1፥16 መዘዝ አድርገን ብንመለከት ይሄኛው በተወሰነ ደረጃ የፍጥረተ ዓለም ፈጣሪ፣ ገዢ እና አስተዳዳሪ የሆነው አምላክ በምን እና ለምን ምክንያት፣ ለምንስ ፋይዳ "እንዋቀስ" ብሎ ለእስራኤላውያን ጥሪውን አንዳቀረበ ሐሳቡ ከተለያየ አቅጣጫ ትንታኔ የሚያስፈልገው እንደሆነ አንገነዘባለን።

ያግሞም በማቴዎስ 5፥4 ላይ "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ" የሚለው ትዕዛዝ በእኛ ሰዋዊ ደካማ ተፈጥሮ እንዴት ተደርጎ ሊተገበር ነው? ይህ ደግሞ ሰፊ ሐተታ እና ማብራሪያ የሚያሻው ነው። የለው ልጅ እንደት አንደ እግዚአብሔር ፍጹም ይሆናል? ለመሆኑስ ይሞከራል ወይ?

እንዲህ፣ እንዲህ እያልን ብዙ ጥያቄዎችን ማንሣት እንችላለን። ርግጥ ነው ሰው ያደርገው ዘንድ የማይችለውን አግዚአብሔር እንዲተገብረው አይጠይቀውም፤ ወይም አንድ የወንጌል አማኝ ይሆን ዘንድ የተገባውን በቃሉ ደረጃ ሆኖ እንዲኖ ጌታ ያለ ጸጋው (ያለ ማስቻል ኃይሉ) ለብቻው አይተወውም፤ እንዲችል ያስችለዋል አንጂ።

አንዲህ ካሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦች ውስጥ፣ በቃሉ መሠረት ግልጽ ሠያረግ ካለባቸው እና ከርስቲያናዊ ምላሽም ከሚጠበቅባቸው ውስጥ አንዱ "እግዚአብሔርን መምሰል" የሚለው ነው። ይህ አስገራሚ ነገር ነው። አንድ ከርስቲያን እንደት ያለ የጥዘ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ቢደርስ ነው አግዚአብሔርን መምሰል ሠሚችለው?

አማኝ እግዚአብሔርን ሊመስል ይችል ዘንድ እንዳች ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል ሠለበለ ይኖርበት ይሆን? ወይንስ ለመምሰል እንደ አንድ ትጉህ አትሌት በየዕለቱ

የሚተገበሩ ተግባራት አሉ? ደግሞስ ለስንት ቀን ያህል? ስንትስ ዓመት ይፈጃል ለመሆኑስ እግዚአብሔርን መምሰል በእውኑ ሊሆን የሚችል ነገር ነውን? ወይ ተግባራዊ እናደርግ ዘንድ የተጠየቅነው ይህ እግዚአብሔርን የመምሰል ነገር እንፈጽመዉ ዘንድ የማንችለው ይሆን ወይ? ከተቻለስ እንዴት፣ ምንስ እያደረግን ነው የምንሆነው እግዚአብሔር ራሱስ ምን ይመስላል?

እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እየተነተንን ለማየት የምንሞክረው ይህን ዐቢይ ጭብጥ ነው። በተለይ የመጀመሪያውን የጢሞቴዎስን መልዕክት በደንብ ካስተዋልነው በውስጡ በተደጋጋሚ የተጠቀሰውን ይህን ሐሳብ እናገኛለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ አንደኛ እና ሁለተኛ የጢሞቴዎስ መልዕክትን የጻፈዉ በእምነት ልጁ እና የአገልግሎት እጋሩ ለሆነው ለወጣቱ ጢሞቴዎስ ነው። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት አማኞች በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሕይወት እና በአገልግሎት እንዴት መመላለስ እና ማገልገል እንደሚገባቸው መመሪያ የሚሰጡ ደብዳቤዎች ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልዕክቱ ላይ ከዘጠኝ ጊዜ በላይ እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ጉዳይ ለጢሞቴዎስ ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ደጋግሞ ጽፎለታል። የሚከተሉትም ጥቂቶቹ ናቸው።

- "እንግዲህ *ለማዘለአብሔርን በመምሰልና* በጭምተኝነት ሁሉ ጸጥ እና ዝግ ብለን እንድንኖር. . ." (2፥1-2)።
- *"እግዚአብሔርንም የመምሰል* ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው" (3፥16)።
- *"እግዚአብሔርን ለመምሰል* ግን ራስህን አስለምድ" (4፥7)።
- *"እግዚአብሔርን መምሰል* ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" (4፥8)።
- "ለገዛ ቤተ ሰዎቻቸው *እግዚአብሔርን መምሰል* ያሳዩ ዘንድ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው" (5፥4)።
- "ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና *እግዚአብሔርን ለመምሰል* በሚስማማ ትምህርት. . ." (6፥3)።

ጳውሎስ ይህንን ቃል ደጋግሞ ከተናገረው ነገሩ በጣም አስፈላጊ እና የከበረ ሞጎ ያለው እንደሆነ መገንዘቡ አዳጋች አይሆንብንም።

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ትምህርት በሚኖዛበት ጊዜ በጌታ አምነኖ ለዳነ አዲስ፣ ለተወለደ ክርስቲያን የሚሰጥ የመጀመሪያ ትምህርት አድርገው ነው የሚወስዱት። ይሁን እንጂ መልዕክቱ የተጻፈው ግን ለአዲስ አማኝ ሳይሆን በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት ለሚያገለግል ወይም በጊዜው አገልጋይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሠሪ ሆኖ ያገለግል ለነበረው ለጢሞቴዎስ ነው። ይኄ በራሱ ርዕሰ ነገሩ የላቀ እንደሆነ ያሳያል ብዬ አምናለሁ።

በሌላ አገላለጽ በርካታ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰሉ እርሱን ስለ መከተል ትምህርት ሲሰጥ ይህንን ትምህርት "መልካሙን እና ከፋን ለመለየት በሥጋቸው የለመደ ልቦና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች" የሚሰጥ ጠንካራ ምግብ (ዕብራውያን 5፥14) ሳይሆን፣ ገና ጡት ለሚጠቡ መንፈሳዊ ህፃናት የሚሰጥ ወተት አድርገው ነው የሚቆጥሩት። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳችንን በደንብ ፈትሸን ካየነው ግን ከዘፍጥረት ሦዕራፉ አንድ እንሥቶ እስከ ዮሐንስ ራእይ የመጨረሻው ምዕራፍ ድረስ የሚናገረው እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ነው። ከዚህ የተነሣ ይህ ትምህርት እጥንት ያለው ጠንካራ ምግብ ነው ማለት ነው። በደንብ ካስተዋልነው እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር እና አሾሃም ሁላችን ወደ መኖር ሳንመጣ በፊት በእርሱ ዘንድ በተደረገ መለኮታዊ ምክር ውስጥ የነበረው ድንጋጌ ለው የልጁን መልክ ይመስል ዘንድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን እንዛመስል!

ይህ ውሳኔ ይህች ዓለም ሳትፈጠር፣ ሁላችንም ወደ ምድር ሳንመጣ እግዚአብሔር የወሰነው ውሳኔ ሲሆን፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉም የወሰነበት ነው (ሮሜ 8፥29)።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር *"ሰውን በመልካችን ለንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" (ዘፍጥረት 1፥26)* ብሎ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ሰውን ካለ መኖር ወደ መኖር ሲያመጣው የልቡ ሐሳብ እና ዕቅድ የነበረው የእርሱ መልክ እና አምሳያ ያለው አድርጎ መፍጠር ነበር። የወንጌል አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግመኛ የተወለድነው እና በእግዚአብሔር ዘንድ የምናድገው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንመስል ዘንድ ነው። በኋላ ላይ ጊዜ ሲመጣ፣ የምንከብርበት ሰዓቱ ሲደርስና ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወዳለበለት

ፍጻሜ ደርሶ በቅጽበት ዓይን ስንለወጥ ኢየሱስን እንደምንመስል ዮሐንስ በመልዕክቱ *"ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠ። ዳሩ ግን ሲገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንደንመስል እናውቃለን"* (፩ ዮሐ 3) ብሎ ነግሮናል።

እግዚአብሔር እርሱን እንድንመስለው ወሰኖ ሲፈጥረን በመልኩ እና በአምሳ ነው። የእርሱን መልክ እና ምሳሌነታችንን ኃጢአት ባበላሸብን ጊዜም እንደገና በክርስ ዳግመኛ የወለደን ልጁን እንድንመስል ነው። ወገኖቼ ሆይ! ዘመን ተፈጽሞ በአዳ ዘላለም መኖር ስንጀምር በዚያን ጊዜ የምናውቀው ዕውቀት ኢየሱስን እንደምንመ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ፣ በጣም ጥልቅ ምስጢር ፣ አጅንዳም ነው። ስለሆነም እግዚአብሔርን መምሰል ሰው በዘመኑ ሁሉ ወ የሚመገበው ጽኑ ምግብ አንጂ የህፃንነት ትምህርት አይደለም።

በወንጌል በጣም ደስ የሚለኝ ነገር ወንጌልን የተቀበልኩበት፣ አገልግዬም እ ፍጻሜ መሄድ የምፈልግበት ምክንያት እግዚአብሔር የዓለምን ጥበበኞች የሚያሳፍርበ ጥበብ አድርጎ ስለገለጠው ነው። ደግሞም ማንም የማያስተውለውን ህፃናት ናቸ የተባሉት ይቀበሉት ዘንድ እንዲገለጥላቸው አቅልሎ መምጣቱ ነው። የባለጠጎችን ሀብ የሚያሰንቅ ውድ እና ከቡር አድርጎ ለእኛ ሊድኽቹ እንዲገባን አድርጎ መምጣቱ ነው እግዚአብሔርን ዘወትር ስለዚህ አመስግነዋለሁ። ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃ ለመስበክ ወይም ለማስተማር ስዘጋጅ ደጋግሜ የማስበው ነገር ቃሉን ለሚሰሙኝ ሰዎ አመላከቼ አንዳላቀርብባቸው ነው። አንዳንድ የቃሉ ሳባኪዎን እንዱን ቃል አርባ ጊ ፈትለው፣ ፈታትለው አንዱን በእንግሊዝኛ ሌላውን በአማርኛ ጮማይደው፣ የጠፊው እና የከተሜውን ቃላት ጨማምረው ከልሰው እና እውተፍትፈው ሲያወላስቡ መስማት ያስመርራል፤ ደግሞም ያስፈራል።

የምሥራቹ ቃል ወንጌል እንዴት በተወላሰቡ ቃላት ታጅሎ ይቀርባል መልካም የሚሆነው ቀለል ባሉ ቃላት ለአድማጩ ሕዝብ ሲቀርብ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል *"ባለረሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እን ለእንዲጠፉ ለማዘአብሔር እንድያ ልጁን ለስኪለጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና (ዮሐንስ 3፥16)* ይላል። ሰው ሁሉ ቃሉን እንደ ተጻፈው ሰምቶ እንዲረዳው ማድረግ ትልቅ ቁም ነገር ነው። እግዚአብሔርን የመምሰል ነገር ልጁ ዋጋ የከፈለበት እንጂ ዝም

ብሎ የህጻንነት ትምህርት አይደለም። አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ደግሞም የከበረ ይህ ሐሳብ፣ ዘመናችንን በሙሉ ልንከተለው የሚገባን፣ አሁንም ያለ እና ወደፊትም የሚፈጸም አጅንዳ ነው። ይገርማችኋል! የሰይጣንን ሐሳብ በደንብ ከፈተሸነው ዓላማው ይሄንን ማበላሸት ነው።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እንደሚናገሩት በዘፍጥረት ፩፡፭ ላይ *"ምሽርም ባደ ነበረች፤ ለንዳችም ለልነበረባትም፣ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር"* የሚለውን ቃል መሠረት አድርገው እግዚአብሔር ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ በፊት ሌላ የሰራው ዝብርቅርቅ ያለ፣ መልክ አልባ፣ ጨለማ የሰበሰ ዓለም እንደነበረ ያስባሉ። ስለዚህም ይሀንን ዓለም ሊገለጠው፣ ያሰማምረው እና ያበጃጀው ጀመረ። ይሁንና እግዚአብሔር ያንን የተበላሸውን ነገር አስተካክሎ አበጃጅቶ፣ ገትን ፈጥሮ፣ ሰውንም በመልኩ እና በአምሳሉ ፈጥሮ ሁሉንም ነገር በትክክል ሠርቶና አጠናቅቆ ከሥራው ሲያርፍ፣ ሰይጣን መጥቶ አንደገና የተሠራውን አበላሸው።

አሰኪ በዙሪያቸሁ ያሉትን የሰው ልጆችን ሕይወት በጥሞና ተመልከቱት። ነገሮች ሁሉ የጤና አይመስሉም። ውል አንደ ሌለው፣ ውጥንቅጡም አንደ ወጣ ልቃቂት ሱጠሮ ቢመዙት ቢመዙት የማይፈታ ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ ከልጅ እስከ አዋቂው፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሲታይ አንዳች የተበላሸ ነገር ሳይኖርበት አይቀርም!

ቴሌቪዥን ከፍታችሁ ዜና ብትሰሙ፣ ጋዜጦችን ብታነቡ፣ ዝም ብላችሁ ጎረቤቶቻችሁን ብታዩ ነገሮች ደኅና አንዳይደሉ ትገነዘባላችሁ። አንድ የተበላሸ ነገር መኖሩን ለማወቅም አይከብዳችሁም። ጦርነት የሚባለው ሌላው ጭካኔ የተሞላበት ይብዱ የሚያሳቁለውን የተበሰከሰከ ሰው አይታችሁ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው እንዴት አንደ ተበላሸ ማወቅ ትችላላችሁ።

የአእምሮ ችግር ኖሮባቸው ርዳታ ወደሚያገኙበት የአእምሮ ሕመማን ማገገሚያ ሆስፒታል የገቡ ሰዎችን ስመለከት ልቤ እጅጉን በጎዘን ይሰበራል። አነዚያን ሰዎች በዓይኔ አይቼ "ከቡር የሆነው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው እንዴት ተበላሸ?" አላለሁ። ራሳቸውን መግዛት ሲሳናቸው፣ አርቃናቸውን ሆነው ስለሚናገሩት ነገር ማስተዋል ሲያቅታቸው ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ፭፡፩-5 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሰው ገላቸውን ሲቦጫጭሩ፣ ሲፍቁ ወይም ራሳቸውን ሲጎዱ

ስመለከት "እቤቱ እምላከ ሠይ ከቡር የሆነው አምላልህ የሰው ልጅ ምንኛ ተበላሽቷል?" አላለሁኝ።።

ይሁንና እዚያ ብቻም አይደለም፣ በአካባቢያችሁ ወጣ ብላችሁ ስውን ሁሉ ብትመለከቱት ለመሆኑ ማን ነው የተበላሸ መልከ ያልያዘው? ለመሆኑ የዚህ ችግር መንስዔው ምንድነው?

የሰው ልጅ ይህን ዓይነት የተበላሸ መልከ እንዲኖረው ያደረገው ሰይጣን ነው።። ሰይጣን ተነሣሽነቱም ሆነ ዕቅዱ እግዚአብሔር የሠራውን ማበላሸት ሲሆንኝ የእግዚአብሔር አጅንዳ ግን የበለጠ አስውቦ እና አሰማምሮ መሥራት፣ የተበላሸውንም ቀድሞ ወደ ነበረበት ከብሩ መመለስ ነው።። ስለዚህ እኔም በዚህች መጽሐፍ አግዚአብሔርን መምሰል ስለ መቻል ጉዳይ አወራችኋለሁ።።

መልካም ንባብ!

በድሉ ይርጋ (ዶ/ር)

ምዕራፍ 1

እግዚአብሔርን ምሰሉ!

ምዕራፍ አንድ

እግዚአብሔርን ምሰሉ!

፩. እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው?

መጀም አንድን ነገር ከመምሰላችን በፊት እንመስለው ዘንድ ስለተገባን ሰለዚያ ነገር ማወቅ ይኖርብናል። የማታውቁትን ነገር በፍጹም መምሰል አትችሉም። ቀድሞ ነገርም አትሞክሩትም። በፍጹም የማናውቀውን፣ በዓይናችን ያላየነውን ሰው መምሰል እንችልም። ለመምሰል የምንሞክረው እና መምስልም የምንችለው በዓይናችን ያየነውን፣ በጆሯችን የሰማነውን እና በመረጃ ያወቅነውን ነው።

ልጆችን ሲታዩዋቸው ወንዶቹ በአባታቸው፣ ሴቶቹ ደግሞ በእናታቸው ጫማ ውስጥ እግራቸውን በመከተት ወላጆቻቸውን ለመምሰል ይሞክራሉ። ለምንድነው ያንን ለማድረግ የፈለጉት? አባታቸው ወይም እናታቸው ጫማውን ሲጫሙ ስላዩ፤ እነርሱኑ ለመምሰል ነው። አንድን ነገር ለመምሰል የግድ የሚታይ ነገር መኖር አለበት። አንድን ነገር ካዮችሁት በኋላ ነው፤ ያንን ነገር ማግኘት ወይም መምሰል አፈልጋለሁ የምትሉት። ያ ነገር ከሌላችሁ ግን መምሰል የሚለው ሐሳብ ከወዴት ይመጣል?

ሰው በልቡ የተማረከለትን፣ በስሜት የተሸነፈለትን፣ በአለባበሰ ቢሉ በአረማመድ፣ በአነጋገር ይሁን በድርጊት፣ በጠባይ ሆነ በሙያ እንዲያው በደፈናው ልቡን ኮርኩሮ፣ ስሜቱን ቆንጥጦ የያዘውን ነገር ለመምሰል መሞከሩ ተፈጥሯዊ ነው።

አንድ ወቅት ላይ ልጆች ቤት ውስጥ "ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን እንሥዒወት" ተባባሉ። ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሰዎች በዚያ ሲዘምሩ፣ ሰባኪያኑ ሲሰብኩ ወይም ሲያሰተምሩ ተመልከተዋቸዋል። በጨዋታቸውም ውስጥ አንዱ ተነስቶ ሲዘምር፣ አንዱ ቆሞ ሲሰብክ፣ ሌላው ደግሞ የአምልኮ መሪ ሆኖ ቀረበ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲከናወን ያዩትን ለመምሰል እየሞከሩ ሳሉ ድንገት አንድ ችግር ተከሰተና በመከከላቸው ሜሜሜታ ተፈጠረ። የዚህን ጊዜ እናት የልጆቿን ጩኸት ሰምታ ሮጣ ሰትወጣ አንደኛው

ልጅ ድመቷን ውሃ በሞላበት ሳፋ ውስጥ እየዘፈቃት ትደርሳለች። ለካስ ልጅ ድመቷን የውሃ ጥምቀት እያጠመቃት መሆኑ ነበር።

ልጆቹ ይህን ያደረጉት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲደረግ ያዩትን ለመምሰል ሰለፈለጉ ነበር። ስለዚህም ያዩትን እና የሚያውቁትን ወደ ተግባራዊ ልምምድ ወሰዱት።

ወደ ተነሣንበት ርዕሰ ጉዳይ ስንመለስ መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር መምሰል" የሚለውን የጥሩ ክርስትና ሕይወት ልኬት አድርጎ ካስቀመጠው እና እሳን ሕዝብ ሊለማመደው እና ሊሆነው የተገባው ሆኖ ካቀረበው በቅድሚያ ይመስለው ዘንደ የተገባው እግዚአብሔር ሊታወቅ ይገባል። በእጭሩ እግዚአብሔርን ለመምሰሬ እግዚአብሔርን ማወቅ ግድ ይላል።

እያችሁ፤ እግዚአብሔርን ለመምሰል እግዚአብሔርን ማወቅ ይጠይቃል፡ አለበለዚያ ምኑን፣ እንዴትስ አድርገን ነው የማናውቀውን ነገር የምንመሰለው? ለመሆነ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሱ እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ እግዚአብሔር የሚገልጸው ነገር፤ እግዚአብሔር ማንም ሊያየው በማይችል ብርሃን ውስጥ በዘላለም ክብር የሚኖር አምላክ መሆኑን እና ማንም እርሱን አይቶ በሕይወት ሊኖር እንደማይችል ነው። ይኼንን አምላክ ምን ብለን ነው የምንመሰለለው? ይኼ ራሱን የቻለ ትልቅ ጥያቄ ነው። ሆኖም ዘፍጥረት 1፡26-27 *"እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር የባህር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሶትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው"* እንደሚል ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው። ታዲያ ሰው እግዚአብሔርን እንዳያይ እና እርሱን እንዳይመስል የገጠመው ችግር ምንድነው? ሰው በኀጢአት ስለወደቀ እና ኀጢአት ይህንን መልካችንን ስላበላሸብን አሁን የተበላሸ መልከ ነው ያለን። እንኳንስ እንደዚህ የተበላሸ መልከ ይቅርና እውነት እንኒገር ካልን የራሳችንን የድሮ ፎቶ ስናይ እንደነግጥ የለም እንዴ! ለምን? ምክንያቱም አሁን መልካችን ተለውጧል! ሰው፤ ሰውን አይቶ እግዚአብሔርን መረዳት እንዳይችል መልኩ፣ ሕይወቱ ተበላሽቷል። ውስጡን እኔነት፣ ኩራት፣ ትዕቢት፣ ጭካኔ፣ ግድያ ሰለሞላው በእዝህ ሁሉ ተሸፍኖ ነው ያለው። ታዲያ ምን ይሻላል?

በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው እንዲህ ከተበላሸና እግዚአብሔርን ማየት ካልቻለ እንዴት ነው እግዚአብሔርን የሚያየው? ካላየውስ እንዴት ነው እርሱን መምሰል የሚችለው?

መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 1፡18 ላይ *"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው ለኔና ሰንኳ የለም፣ በአባቱ ለቅፍ ያለ ለንድ ልጁ አርሱ ተረከው"* ይለናል። ተረከው ማለት "ሰበከው፣ አሳየው፣ ገለጸው" ማለት ነው።

በዕብራውያን 1፡3 ላይ ደግሞ "አርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ. . ." ይለናል። የእግዚአብሔርን ነጸብራቅ የሚያሳየን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው።

ሰው መልኩ ጠፍቶ እንዲሁ እንዳይቀር እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከለት። እርሱን ያየ እግዚአብሔር አብን ማየት እንዲሆንለት ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መጣ። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ አንድ የሚገርም ጥያቄ እና መልስ አለ። ያም ፊልጶስ *"ጌታ ሆይ ለብን አባየንና ይበቃናል"* ሲል የጠየቀው እና ኢየሱስም *"አንተ ፊልጶስ ይሀን ያህል ዘመን ከለናንተ ጋር ሰናር ሊታወቁኝምን? ለኔን ያየ ለብን አይቶአል"* ብሎ መለሰለት።

ሰው እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አውቆ እግዚአብሔርን መምሰል ነፈለገ ምስጢሩ ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ደግሞ ሥጋላል። የእግዚአብሔር ቃል በ1 ጢሞቴዎስ 3፡16 ሲናገር *"እግዚአብሔርንም ሥመምሰል ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፣ በመንፈስ የጸደቀ፣ ለመላዕክት የታየ፣ በአህዛብ የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ"* ብሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገራል።

ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል የምንችልበት ትክክለኛ ምሳሌ እና ነጸብራቅ አለን ማለት ነው። የምስራች! እግዚአብሔርን ማየት እንችል ዘንድ አንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶልናልና በጎዘን ቆዝመን ልንቀመጥ አይገባንም። የሰው ልጅ ለሆነው ለእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁንለት!!

ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ኢየሱስን መምሰል ማለት ነው። ኢየሱስን መምሰል ደግሞ ኢየሱስ እንደሚናገረው መናገር፣ እንደሚያደርገው ማድረግ፣ አሪሱ የሚያዘውትረውን ነገር ማዘውተር ማለት ነው። የማናውቀውን ሰው ልንመስለው

ባንችልም፣ የምናውቀውን ኢየሱስን መምሰል ግን እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ሰዉ ሲዘምር ወይ ሲያስተምር ወይ ደግሞ አንድ ነገር ሲያደርግ አይታችሁት "ይህን ሰዉ የማውቀው ይመሰለኛል" ትላላችሁ፤ ምክንያቱም ያንን ነገር የሚያዘወትር በዚያ ደረጃ የምታውቁት ሰው ስላለ ነው። ይሄኛው ሰው መጥቶ ያንን የሚያደርግ በሚመስላችሁ ጊዜ ይሄን ሰውዬ ትታችሁት ሌላ ሰው ትፈልጋላችሁ። ማንን ነው የሚመስለው ትላላችሁ። አንዳንድ ጊዜ የሆነ ሰው ሲያስነጥስ እንኳን "እገሌን ይመስለኛል" እኔ የለም እንዴ? ያ ሰው ሌላን ሰው እንድታስታውሱት የሚያደርጋችሁ የሆነ ነገር አለዉ ማለት ነው።

2. እግዚአብሔርን መምሰል ለምን ይጠቅማል?

ኢየሱስን በማየት እግዚአብሔርን መምሰል የሚቻል ከሆነ እግዚአብሔር መምሰል ለምን ይጠቅማል? ለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ለወለደው ልጁ ለጢሞቴዎስ በ1 ጢሞቴዎስ 4፥7-8 የተጻፈውን እንዲህ የሚለውን ቃል እንመልከት፡ *"ነገር ግን ሰዚህ ዓለም ከሚመኙና የሐሮሚቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረፈ ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አሰለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነዝ ማሰለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል"* ይላል።

እግዚአብሔርን ስለ መምሰል አንድ ምሳሌ ልውሰድና ላላያቸሁ። የስፖርት እንቅስቃሴ ማዕከል (ጂም) መግባትና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መስራት የስፖርት ቋንቋ ነው። ጂም ገብቶ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በመሥራት ሰውነትን ማሰለመድ ለዚህ ለምድር ሕይወት ይጠቅማል። እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ ሚድረግ ግን ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ይጠቅማል። በዚህ ቃል መሠረት እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ ሁለት ጥቅም አለው ማለት ነው። አንዱ አሁን በምድር ለምንኖረው ሕይወት፤ ሁለተኛው ደግሞ ለሚመጣው ሕይወት።

ለሚመጣው ሕይወት የሚጠቅመን ምንድነው? ወገኖቼ ሆይ በቤተ ክርስቲያን የአባልነት መታወቂያ ካርድ መንግሥተ ሰማይ አንገባም። የእግዚአብሔርን መንግሥት የምንወርሰው አዚህ በቤተ ክርስቲያን በምናሰመዘግበው ውጤታማነትም አይደለም። መንግሥተ ሰማይ የሚቀበለን የተፈጠርንበትን፣ ዳግም የተወለድንበትን እና ተስፋችን

የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስንመስል ነው።

የዘላለማዊ ርስት ከብር ተካፋዮች የሆንነው እግዚአብሔር አብ፣ በብዙ ዘሃይማኖቶች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ ባደረገው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። ያንንም ርስት የምንካፈለው ኢየሱስን በመምሰል አንጂ በሌላ ማንነት አይደለም። ይህ ኢየሱስን ወይም እግዚአብሔርን መምሰል የምንለው ትምህርት ለአሁኑ ዘመንስ ምን ያገለግላል? በክርስትና ሕይወታችን ከቶውኑ ወደ ጎን ልንገፋውና አሌ ልንለው የማንችለው ግዙፍ ጠቀሜታ አለው። በምድራዊ ሕይወታችን ከእግዚአብሔር ጋር የሰመረ ጎብረት የሚኖረን ዕለት ዕለት እግዚአብሔርን በመምሰል ሕይወት ለመመላለስ የዘነጋን እንደሆነ ብቻ ነው። አሁን በአፀደ ሥጋ በዚህ ምድር ስንኖር በጸሎት፣ በቃሉ እና በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው ግንኙነት ስኬት የሚኖረው እግዚአብሔርን መምሰል ካለ ብቻ ነው። በአገራችን "ሳል ይዞ ሰርቆት፣ ቂም ይዞ ጸሎት" የሚል ምሳሌያዊ አባባል አለ። አስገራሚ ንጽጽር ነው።

እግዚአብሔርን ስለ መምሰል የምንማረው ትምህርት እና እርሱን በመምሰል የሚመላለለው ሕይወት በምንጸልየው ጸሎት ውስጥ ዐቢይ ስፍራ አለው። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ 19 ላይ የተጠቀሱት የአስቄዋ ልጆች ታሪክ ለተግሳጻችን የተጻፈልን ነው። *"ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ሰም እናምላቸዋለን" (ቁጥር 13)* እያሉ ከቶዎች ኢጋንንትን ባሉባቸው ሰዎች ላይ የኢየሱስን ሰም ሲጠሩባቸው ኢጋንንቱ ምን ነበር ያላቸው? *"ኢየሱስን አውቀዋለሁ፣ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ አናንተስ ለምማን ናቸሁ?"* ነበር ያላቸው *(ቁጥር 15)*። በሌላ አገላለጽ ማንን ነው የምትመስሉት? ማለቱ ነዘር። መልከ፣ አምሳያችሁ ማንን ይመስላል? ብሎ ርኩሱ መንፈስ አነኚህን የአስቄዋን ልጆች መረመራቸው። ትልቅ ከሰረት እና ውድቀትም ገጠማቸው።

በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔርን በመምሰል በጭምትነት እና በበጎ ጎሊና የሚመላለለ ቢሆን ከቶውኑ ምን የሚያሰፈራን ነገር አለ? ይህንን ነው በዚህ ምድር በሥጋ ሕይወት ስንኖር ሳለን ጥቅም እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን። በርግጥም እግዚአብሔርን መምሰል ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት የሚጠቅም ስለሆነ ምንም የሚያሰፈራን ነገር የለም።

"ይጠቅማል የምትሉትን ሁሉን ነገር ውሰዱና ጻፉ" ቢባል የምንዘረዝረው ነገር ምንባባት በምድር ላለው ነገር ረብ ይኖረው ይሆናል። ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ ረብ

ያለው፣ የሚተርፍ፣ የሚጠቅም ነገር ያለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል ብቻ ነው። ወደ ሦስተኛው ነጥቤ ከመግባቴ በፊት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ" ብሎ ያዘዘውን ትዕዛዝ በተመለከተ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ማያያዝ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም "እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ" የሚለው ቃል ሥራ መሥራትን እሊያም ተግባራዊ ምላሽን የሚጠይቅ ስለሆነ "ጸጋን እንድንጥል እያስተማርከን ነው" ሊሉ የሚችሉ ወገኖች ስለማይጠፉ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ማቅረቡ ተገቢ ነው።

የዳንነውም ሆነ የምንድነው በአምነት በክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ ብቻ እና ብቻ ነው። በዚያ ውስጥ የሰው አስተዋጽዖ የለበትም፤ ሊኖርበትም አይችልም። ነገር ግን በአምነት፣ በጸጋው የዳነ ማንም ሰው ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን እየመሰለ መሄድ፣ ማደግ እና መለወጥ አለበት። ይሄ ደግሞ የእኛን የግል ጥረት የሚያካትት ጉዳይ ነው። ሰው በዚህ ውስጥ ድርሻ አለው። በመዳኔ ውስጥ ድርሻ የለኝም፤ ነገር ግን ድነትን ከተቀበልኩ በኋላ በዚህ እግዚአብሔርን እየመሰልኩ በምኖርበት መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እያደግሁ ለመሄድ የእኔ ግል ድርሻ አለበት። በቲቶ መልዕክት ምዕራፍ 2፣11 ላይ *"ለሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና"* ይላል። ይህ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያስተምር ጸጋ ነው። የሚያስተምረንም ራስን መካድ፣ እግዚአብሔርን መምሰል፣ ክርስቶስን በናፍቆት መጠባበቅን ነው።

ይህ ጸጋ ዕለት ዕለት በልምምዳዊ ሕይወት ተጠምደን መመላለሰን እና መገስገስን የሚያስተምረን፣ ከዚህ ላቅ ሲልም እግዚአብሔርን የመምሰል ተግባራትን እያከናወንን መልኩንም እየተላበስን ፍጹም እርሱን መምሰል ወደምንችልበት እርከን ለመሸጋገር የሚያበቃን ጸጋ ነው። በዚህ እግዚአብሔርን እየመሰልን በምንጓዝበት የቅድስና ጉዞ የእኛ ድርሻ በእጅጉ አለበት።

ጳውሎስ "ራስህን አስለምድ" በማለት የተጠቀመበት ቃል ከጂም ስፖርት ቤት ወይም ከወታደር ቤት ቋንቋ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ራስን ማስለመድ ሰውነትን በአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንደማሠልጠን እና እንደ መግራት ተግባር ያለ ሲሆን፣ ወጣት አትሌቶችን ለኦሎምፒክ ውድድር እንደማዘጋጀትም ሆኖ ሊታይ ይችላል።

ልክ እንደዚሁ በአምነት፣ በጸጋው፣ የዳነ እና ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ዳዴ ሲል ሰንበቶ ድከ ድከ እያለ መራመድ ሲጀምር እና በሰምሶማ ለመሮጥ ሲበቃ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ደረጃ በደረጃ እንደ አቅሙ መጠን ያለ ሐኬትና መሰልቸት በትጋት የሚያከናውናቸው፣ የእርሱ የግሉ ብቻ የሆኑ ተግባራት አሉት። ያ ነው በዝግታ የእግዚአብሔርን መልክ እየተላበሰ እንዲሄድና ደግሞም እንደ አትሌቶቹ የክርስትና ሩጫውን በድል አድራጊነት እንዲያጠናቅቅ የሚያደርገው።

በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔርን መምሰል የእያንዳንዳችን የግል ኃላፊነት ነው። እግዚአብሔርን ለመምሰል ከፈለግሁ ማንም ሰለ እኔ እግዚአብሔርን አያመሰልልኝም። እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት በምስለኔ ወይም በእንደራሴ ውነልና ሊወከል አይችልም። የእኔ የግል ኃላፊነት ነው የሚሆነው። የእኩል ብቃት እንትስቃሴ ወደሚሰራበት ጂምናዝየም ስትሄዱ ማንም ሰው ወደ እናንተ ቀርቦ "እባክህ ዛሬ አልተመቸኝም፤ ጂምናዝየም መምጣት ስላልቻልኩ ከሥራ ስትወጣ በዚያው ሄደህ ሰለ እኔ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሥራልኝ" አይላችሁም። ለምንድነው የማይለው? ጂም የሚሠራው በግል ለግል ሰለሆነ ነው። እግዚአብሔርንም መምሰል እንዲሁ ነው። ማንም ሰለ እንተ፣ ለለ እኔ፣ ስለ እንቺ፣ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን አይመስልልንም፤ ከቶውኑ!

ጌታ ኢየሱስ ከርሰቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14፣27 ላይ ሲናገር *"ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም"* እንዳለው እንዲሁ እግዚአብሔርን መምሰል በየግላችን የምንለማመደው የየግል ኃላፊነታችን እና ተግባራችን ነው።

ሌላው በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው ነጥብ "ራስን ማስለመድ" የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በውስጡ ግብ ወይም ዓላማ ያለው የመሆኑ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን የማስለመድን ያህል ብርቱ ተግባር፣ ረቂቅ ግና ግዙፍ በሰው ሕይወት ላይ ለሊሎች ሊታይ እና እንደ መጽሐፍ ሊነበብ የሚበቃ የላቀ መንፈሳዊ ሕይወት ከኑውኑ እንደምን ያለ አንዳች ግብ ወይም ዓላማ ሊከናወን እና ውጤት ሊታይበት ይችላል!? ከውለጣዊ ግፊት የሚፈጠር እንደ አሳተ ገሞራ ፍንዳታ ያለ ግብ እና ዓላማ ሰኖር ነው። ከውጪ የሚታይ ርግጥነት ያለው ዓይንን እና ቀልብን የሚሰብ ምስለ-እግዚአብሔር የሚታይበት ሕይወት መኖር የሚቻለው በውስጣችን ጽኑ ግብ እና ዓላማ

ሲኖር ነው።

አግዚአብሔርን በመምሰል ሕይወት ልምምድ እና ራስን ለዚህ ተግ በማስገዛት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው ግብ አግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ፣ አ የሚቆጣጠረውና በእርሱ ሐሳብ ዙሪያ የሚሽከረከር ወይም የሚያጠነጥን ሕይው ለመምራት ቁርጠኝነትን እና ፍጹማዊ ፍላጎትን ማሳየት ነው።

ሁለተኛው እና ከዚሁ የሚለርፀው ደግሞ በውጪያዊው የሕይወት እንቅስ ውስጥ አግዚአብሔርን ለመምሰል በግብር የሚገለጠው እና በይፋም የሚታይ ሕይ ነው። በሌላ አነጋገር የውስጥን ፍላጎት በውጪያዊ ተግባር መግለጥ ማለት ነው። እነ ሁለቱ ሲጣጣሙ እና ሲሰምሩ በልባችን፣ በሐሳባችን ውስጥ አግዚአብሔርን መም ይሆንልናል። አግዚአብሔርን የምመስለው እርሱ በልቤ ውስጥ የሕይወቱ ማዕከል ሲ ነው። በምንወስናቸው ውሳኔዎቻችን ሁሉ አግዚአብሔርን እያስብን መወሰን ሰንዝ በነገር ሁሉ ጌታን ብለን በመምረጥ በቁርጠኝነት እና በጽናትም ለመራመድ ሰንዝ ያንጊዜ ፋይዳው የከበረ ዓላማ እና ግብ ኖሮን ለዚያው ዓላማ እና ግብም እየኖርን ነ ማለት ይቻላል።

ምርጫ እና ሐሳባችን ሁሉ በእምላካችን አተያይና ፈቃድ ብቻ ሲሆን ያንጊ በጥሩ ቀራጭ እጅ እንዳለ እና በዝግታ የጊዜ ሂደት እየተጠረበ፣ እየለዘበ፣ ሊያማረ ነ እየተዋበ ቀልብ ሳቢ ምስል እየተከሰተበት እንደሚመጣ ዐለት ጌታችንን እየመሰለ እንሄዳለን። በምርጫዬ፣ በውሳኔዬ ውስጥ ጌታን ስሾም፣ ለምች "ደግሞ እሁን እዘ ውስጥ ሊየሱስን ምን አገባው?" ሲሉኝ "ያገባዋል!" አላቸዋለሁኝ። ብሞትም፣ በሕይወ ብኖርም በእኔ ላይ ጌትነቱ ገኖ ምሉዕ ልዕልናው እና ሥልጣኑ በእኔ ላይ ተንሰራፍ ሁለንተኛዬን ሲገዛው ያንጊዜ አግዚአብሔር ማዕከል የሆነበት ሕይወት እየመራሁ ነው። በውጪኛው መልካችን፣ አካሄዳችን አነጋገራችንም ጭምር አግዚአብሔር የሚመስል ሕይወት ለንኖር ያንጊዜ ዓላማ እና ግብ ያለው ሕይወትን እየኖርን ደግሞ ግባችንንም እየመታን ነው።

የሐሳቤ ምህዋር በእግዚአብሔር ዙሪያ ሲዘረጋ እና በሁለንተኛዬ የማጠነጥነ በእርሱ ዙሪያ ሲሽከረከር፣ መሽከርከሪያ ዛቢያዬም ሆነ ምህዋሬ ጌታ ብቻ ሲሆን "እንዲያው ይህ የምናገረው ወይም የማደርገው ነገር ጌታን ደስ ያሰኘው ይሆን? የለያ ይቅርብኝ፣ ይሄ ደግ አይደለም!" "ይሄማ አንደ መልካም ዛፍ የጌታ አምላል ባለ ፍሬ

ያደርገኛልና ልግፋበት፤" ወዘተ. እያልኩ ስኖር ለአንዳች ጠቃሚ ግብ እየኖርኩ ነው። በላማ አለኝ፣ ዐላማዬም ከዚህ ደረጃ ያነስ አይደለም።

አግዚአብሔርን መምሰል ማለት ቤተ ክርስቲያን መመላለስ ማለት አይደለም። ርግጥ ነው ቤተ ክርስቲያን መሄድ አንዱ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ይሁንና አግዚአብሔርን መምሰል ግን እኛ በጎብረታችን ውስጥ የምናደርጋቸው፣ የለመድናቸው ነገሮች አይደሉም። እነሱ የሚጠቅሙ ናቸው። ታውቃላችሁ፤ ወንጌል ሰባኪ ወይም አገልጋይ ስለሆንኩ እንዲህ እና እንደዚያ እናድርግ አላችኋለሁ። ነገር ግን አግዚአብሔርን መምሰል የሚጀምረው በልብ ውስጥ ነው። አግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ በውጪ የሚታይ ሕይወት ሲኖረን ነው። ቀደም ሲል ጀም ይሄዳል ያልኳችሁ ያ አትሊት ዐላማ ኖሮት ለራሱ እንደሚሰራው ቢያንስ ለዚያ ነገር መሰጠት አለበት።

ነገሩ ቁርጠኝነት እና መሰጠት ያስፈልገዋል። ዓይኑን ያፈጠጠ፣ ጥርሱን ያገለበጠ ፈተና ሲመጣም ድል ነሥቶ ለማለፍ አግዚአብሔርን ሳይሆን ሌላ እንዳች ነገርን አንድንመስል እና ተጠላልፈን እንድንወድቅ የሚታገለንን በመንፈሳዊ ፍልሚያ ድባቅ እየመታን የሰማዩ እቢታችንን እንመስል ዘንድ ቆራጥ መሆንን ይጠይቃል። ዐላማ እና ግብ ማበጀት እንድ ቀዳሚ ቁም ነገር ነው። መስናከልን እያለፉ ራስን ተወነካከሮ ካለመውደቅ እየጠበቁ፤ ቢወድቁ እንኳ ተፍ ብሎ ተነስቶ ጉዞን ለመቀጠል ቆራጥነት ሊኖር የግድ ይላል። ጽናት ያሻል።

ጀም ስለመሄድ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ስለመሥራት እንሥተን ተነጋግረናል። እንዲያው የእውነት፣ የእውነቱን ለመነጋገር ጀም ሄደን ተመዝግበን፣ አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽመን፣ በሳምንት የተወሰኑ ቀናትን እና ሰዓታትን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረን፣ ያላቋረጥን ስንቶቻችን ነን፣ ደግሞስ እንደገና ተመዝግበን እንደገና ያላቋረጥን? ይህ ከሆነ ችግሩ ያለው የቱ ጋ መሰላችሁ? ቁርጠኝነት እንሶን፣ ጽናትም እጥተን ነው።

ትግሏ ቁርጠኝነቷ ናት። ራሳችንን አግዚአብሔርን መምሰል ማስለመድ ከፈለግን "ይሄን ነገር አደርገዋለሁ፣ አሆነዋለሁ!" የምንልበት ቁርጠኝነት ውስጥ መግባት አለብን። ቁርጠኝነቱ ከሌለ ግን ንግግር ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው። ወገኖቼ ሆይ! የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የራሱ አሠልጣኝ እንዳለው ሁሉ አግዚአብሔርን መምሰልም አስተማሪ ማግኘትን ይጠይቃል። የምንማረውም ከአግዚአብሔር ቃል ሲሆን፣

የሚያስተምረን ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። በተጨማሪም ከፊት ለፊታቸው ፈተኛ ሯጭ በመሆን የአግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩን ሰዎች ስላሉ ከእነርሱዎ መማር እንችላለን። አለምሮን፣ ልብን እና አካሄድን የሚለውጠው ትምህርት እንሃ መሆኑ መጠን፤ ያለ ትምህርት እግዚአብሔርን መምሰል አይቻልምና ለትምህርት ቦታ መሰጠት ያስፈልጋል። አመልጣኝ እንዳለው ሰው የአግዚአብሔርን ቃል ለመማረ ተቀምጬ "ዛሬ መንፈለ ቅዱስ ምን ያስተምረኛል? የአግዚአብሔርስ ቃል ምንድነወ የሚለው?" ብዬ ጀርዬን ሰከፍት ነው ጥሩ መንፈሳዊ ሊፖርት የምሠራው።

አነዚህ ጂም የሚሄዱ አትሌቶች ራሳቸውን ለትልቅ ቁም ነገር የለጡ ሰዎች ናቸው። ወገኖቼ ሆይ! ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በተደጋጋሚ ጊዜ "ከእኔ የሰማኸው ጤናማ ትምህርት ያዝ" እንዳለው ይህን ትምህርት በዚህ ዘመን ለማግኘት በጣም ውደ ሰለሆነ ብዙ ዋጋ ከፍላችሁም ቢሆን አታገኙትም። እውነተኛ የአግዚአብሔር ትምህርት በሁሉም ቦታ የምታገኙት ስላይደለ ያንን ማግኘት ውድ ነው።

ሌላው ነጥብ ምንድነው ያልን እንደሆነ፤ ይህ ጂም ሄዶ የስፖርት እንቅስቃሰ የሚሠራ ሰው ከፊቱ በርካታ ፈተናዎች የተጋረጠበት ለው መሆኑ ነው። "እንዴት?" ቢባል የአካል እንቅስቃሴ በሚሠራበት በዚያ ጂም ውስጥ ብዙ ኩተግባር የሚያዘናጉ ከእንቅስቃሴ የሚያናጥቡ ነገሮች አሉ። የተለያዩ ለለላሳ መጠጦችን በከፍያ የሚተቆ ማሽኖች፣ የመጫወቻ እና ዕረፍት የማድረጊያ ስፍራዎች አሉ። ጎበዝ፥ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሲሠራ የሄደ ሰው ማድረግ ያለበት ነገር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚሠራበትን ማሽን አስነሱቶ አላዩ ላይ ወጥቶ መሥራት ነው ያለበት። አለቀ! ግና ከየማሽኑ ውስጥ ዓይኑ ያማረውን እና ልቡ ያሻውን ለለላሳ መጠጥ እያስፈነጠረ አውጥቶ እየጣረ ወዲያ እና ወዲህ የሚንላወድ ከሆነ ምኑን የሰውነቱን ኩብደት ቀነሰ? ምኑንስ የሰውነቱን ስብ አቃጠለ? ምኑንስ አካሉን አነጸ? እንዲያውም ወደ ጂም ባይሄድ ይሻለው ነበር። ለዚህም ነው "አምቢኝ!" ማለትን እና መጽናትን ቆራጥ እና ቆፍጣናም መሆን ያስፈልጋል የምንለው።

የአካል ብቃት ልምምዱ ይበልጥ መሰጠት እና ቁርጠኝነት እንዲሁም አሠልጣኝም ያስፈልገዋል። አግዚአብሔርን ለመምሰል የተሰጠን ሰዎች መሆን አለብን። ቃሉ "አግዚአብሔርን ለመምሰል ራሰህን አሰለምድ" እንደሚል አግዚአብሔርን ለመምሰል የሚረዱ ነገሮችን ተግባራዊ በማድረግ መማር አለብን። ጳውሎስ

ጢሞቴዎስን "ተለማመድ" እንዳለው መለማመዱን ኩተውነው እርሱን አንመስለውም። እንዲያውም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ስፖርት ለመሥራት ወደ ጂም የሚሄዱ ሰዎች የሚመከሩት ምክር ቢኖር "በል አሁን ሊፖርት በደንብ መሥራት ከጀምረክ በኋላ ሠሥራቱን ያቆምክ ቀን ይህ ሁሉ የተሸከምከው ስብ እንደገና መመለስ ብቻ ሳይሆን አነሳ ሆኖ ነው የሚመጣውና እንዳታቋርጥ" የሚል ነው።

በክርስትና ሕይወታችንም የሚሆነው እንዲሁ ነው። ጂም ውስጥ የአካል እንትስቃሴ የሚሠራው ለው ስፖርቱ የሚጠይቀውን ዲሲፕሊን ጠብቆ እንደሚለራው፣ ለቱነት ወይም ለለምንታት ሥራውን ቢያቋርጥ የፈራው የሰውነት የስብ ክምችት እና አላስፈላጊ ነገር ሁሉ ከቀድሞው በክፉ ሁኔታ ተመልሶ እንደሚያገኘው እና ጅማቶቹም ሙቶሳስር እንደሚጀምሩ ሁሉ፤ አግዚአብሔርን በመምሰል ክርስቲያዊ ልምምድ ውስጥም በኑነበቅ ሥርዓት በታጠረ ጽናት መመላለስ ቸል የሚባል ነገር አይደለም። ዛሬም፣ ነገም፣ ሁሌም የሚያቋርጥ ልምምድ አስፈላጊው ነው።

በስፖርቱ ዓለም ሰፖርተኞች ከውድድር ግጥሚያ በፊት በሚያደርጉት ያላሰለሰ የልምምድ ትጋት በውጤታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው ሁሉም ሚያውቀው እውነት ነው። አግዚአብሔርን መምሰል ራሳችንን በየዕለቱ ለናስለምድ እርሱን እየመለልን በመለወጥ እናድጋለን። ይህ ደግሞ ለጠላታችን ከፍተኛ ሽንፈት ነው። ምነው? ቢባል እንዲህ ያለው መንፈሳዊ ልምምድ ወደ አምላኩችን እና ወደ አባታችን ወደ አግዚአብሔር የምንጠጋጋበት ዓይነተኛ መንገድ ነውና!

ምዕራፍ 2

ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ!

ምዕራፍ ሁለት

ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ!

በምዕራፍ አንድ ላይ የጀመርነውን አሳብ እንቀጥላለን። እንደምታስታውሱ በ፡ ጢሞቴዎስ 4፡7-8 ላይ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አለለምድ ብለ እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ልምምድ እንሥተን እግዚአብሔርን መምሰል ማለ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ በሌላ አነጋገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶ የተናገረውን መናገር፣ ያደረገውን ማድረግ ያዘውትር የነበረውን ሁሉ ማዘውተር ወይ መለማመድ ማለት ነው ብለን ነበር። እንባቢያን ሆይ እንዲህ ያለው ትከከለኛው አይ እንዲኖራችሁ አፈልጋለሁ። ጌታ ራሱ "እናንተ ሸክም የከበደባችሁ ወደ እኔ ኑ፤ ከእኔ ተማሩ" እንዳለን የጌታን ሕይወት አጥንተን እርሱ ያደረገውን ነገር ለናደርግ፣ የተናገረው ለንናገር እና በሄደበት መንገድ ለንሄድ መጨረሻው ቁርጥ እርሱን ወደመምሰ ያመጣናል ብዬ አስባለሁ።

እግዚአብሔርን መምሰል የምንማረው ከእርሱ ነው። የተናገረውን ለንናገ ያደረገውን ለናደርግ በሂደት ኢየሱስን እንመሰላለን። ለዚህ ነው ጳውሎስ በአምነት ልጅ ለሆነው ለጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ እድርግ፣ እነዚህ ነገሮ ይኑሩህ እያለ የሚመክረው።

ይሄንን ልምምድ በተመለከተ ስለ እኔ እኔው አንጂ ሌላ ለል አይደከምልኝም። የዚህ መጽሐፍ መልዕክት ዐላማው ወይም ግቡ እግዚአብሔርን ስ መምሰል ወይም እግዚአብሔርን ማዕከል የሆነበትን ሕይወት ስለ መኖር እንደሆ ተነጋግረናል። ይሄን ለማድረግ ደግሞ መሰጠት እንዳለብን፣ ቁርጠኛ መሆ እንደሚያስፈልግ፣ ሁልጊዜ መለማመድ፣ መማር እንደሚያስፈልገን በምዕራፍ አንድ ላይ ለማየት ሞክረናል።

ታዲያ እነዚህ ደጋግመን የምናደርገውና የምንለማመዳቸው ነገሮች የትኞ ናቸው? በጣም ብዙ ነገሮች ቢያስፈልጉንም፣ ከእነዚህ መካከል በዚህ ምዕራፍ ማንሳት የምፈልገው ወደ እግዚአብሔር መጠጋትን ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር የትኛውንም ነገር ለማድረግ በቅድሚያ ወደ እግዚአብሔር መጠጋትን ልንለማመደው ይገባል። ለምሳሌ ያህል የዚህን ዓለም ሕይወት ቀለል አድርገ ለመኖር የጸሎት ሕይወት፣ ከጌታ የመማር ሕይወት አስፈላጊ ነገር ነው። በዚህ በምኒያባክን ዓለም ውስጥ በጽጥታ መኖርን ልንለማመደው ይገባል። ሌሎችን እያገለገሉ ሣን ነፍሱ መኖርን፣ እግዚአብሔርን የማምለክ፣ ለእርሱ የመታዘዝ፣ የመገዛት እና ቢቀልም ሆነ በኑሮ ለክርስቶስ ምስክር የመሆንን ሕይወት ነው የምንኖረው። በሌላ አነጋገር እርሱ ያደረገውን የማድረግ፣ የሄደበትን መንገድ የመሄድ፣ የተናገረውን የመናገር፣ ያዘወትረው የነበረውን የማዘውተር ሕይወትን ከክርስቶስ ኢየሱስ እንቀስማለን ማለት ነው።

ለዚህ የሕይወት ልምምድ እንዲረዳን ሁልጊዜ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ማድረግ የሚገባን ሁለት ወይም ሦስት ነገሮችን በማንሣት እንነጋገራለን። ስለ ተወዳጅነው፣ ስለ ቀረብነው ለው ለማወቅ የምናደርገው መሠረታዊ ነገር ከዚያ ሰው ጋር የጠበቀ ቁርኝት መፍጠር ወይም መጠጋጋት ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ወደ ጌታ ላይጠጉ፣ ከጌታ ጋር ግንኙነቱ እና ወዳጅነቱ ላይኖራቸው ልዩ ልዩ መንፈሳዊ እገልግሎቶችን ለማገልገል ሲሞክሩ ይለተዋላሉ። እግዚአብሔርን ከመምሰል ይልቅ የሃያማኖተኛነት ካባን ደርቦ መንፈሳዊ ነገርን ማድረግ በጣም ቀላል ነገር ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ላይመስሉ ሃይማኖታዊ ነገሮችን እያከናወኑ እና እየተናገሩ መኖር ይችላሉ። አሁን የምንነጋገረው እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ግን ልምምድን የሚጠይቅ ነው። ይህ የሕይወት ልምምድም ጸሎት፣ ከጌታ እግር ሥር በመሆን ከእርሱ መሠማርና የመሳሰሉት ናቸው። እግዚአብሔር ሁላችንም ወደ እርሱ መጠጋት የምንችልበትን ዕድል ለጥቶናል። ይሁን እንጂ ሁላችንም ይህንን ዕድል በአንድ ወይነት መሰጠት ተጠቅመንበት ተመሳሳይ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ያለን ባለመሆናችን እግዚአብሔርን የማወቅ የእውቀት ደረጃችን ይለያያል።

የአንዳንዱን ሰው ሕይወት ለትመለከቱ በቤተ ክርስቲያን ምስባክ ላይ ቆሞ ሲሰብክ እና ሲያስተምር የማይታይ፣ ነገር ግን ልቡ በአምላኩ የጋለ ፍቅር የቆመ ለው ሊሆን ያችላል። ይህ በመንግሥተ ለማይ የሚታወቅ፣ በሩም ወለል ብሎ የሚከፈትለት

ሰው ሊሆን ይችላል። አንዳንዱ ለሰው መልካም የሚመስል ነገር ግን ሩጫ፣ ግርግ ያለበት ቦታ የሚታጠሩት፣ ጌታ ሲያየው ግን "የቀደመውን ፍቅርህን ጥለሃል፤ ከወዴ አንደወደቅህ አስብ" የሚለው ዓይነት ሰው ይሆናል። ስለዚህ ሁላችንም ወ እግዚአብሔር በመጠጋት ሕይወት አንድ ዐይነት ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ሳይሆን በተለ ደረጃ ላይ ነው ያለነው።

አያንዳንዳችን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ፣ ለመጠጋት ወሳኙ ነገር ፍላጎ እና ልምምድ ነው። ርግጥ ነው የወንጌል አማኞች የሆንን ሁላችንም ጌታችን ኢየሰ ከርስቶስን ስንቀበል የእግዚአብሔር ፍቅር ስጦታ የሆነውና በልባችን የፈሰሰውን መንፈ ቅዱስን ተቀብለናል። ይሄ እንዳለ ሆኖ የዚህ አውነት ሌላኛው ገጽታ ግን አያንዳንዳች አንደ ተቀበልነው መጠን የምንኖረው፣ የምንሰጠው፣ የምናደርገው ድርሻ እንዳለበ ደግሜ ላስገነዝባችሁ አወዳለሁ።

አያንዳንዳችን ከጌታ ጋር የምንኖረው ሕይወት የፈቀድነውን ያህል ነው ይህንን በጌታ ቃል በራሳችን ልናረጋግጠው እንችላለን። ለዚህም ሁለት ምሳሌዎች ላንሣ። የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳኑ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ አሰራኤል፣ የሕዝቡ አለቆ እና እግዚአብሔር ናቸው። እነዚህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን መጠጋጋት አንዴ አንደነበር እንመልከት።

በዘጸአት 19፣10 ላይ *"እግዚአብሔር ሙሴን አለው ወደ ሕዝቡ ሂድ፣ ዛሬ ነገም ቀድሳቸው፣ ልብሳቸውንም ይጠቡ፤ በሦስተኛውም ቀን ሕዝቡ ሁሉ ሲ አግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ። ወሰንም ለሕዝ በዙሪያው አድርግላቸው፦ ወደ ተራራው አንዳትወጡ ጫፉንም አንዳትነኩት ተጠንቀ ተራራውንም የነካ ፈጽሞ ይሞታል፤ የማንም እጅ አይንካ፤ ነገር ግን የሚነካው ሦ ይወገራል ወይም በፍላጻ ይወጋል፤ እንሰሳ ወይም ሰው ቢሆን አይድንም በላቸው* ይላል።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፁ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ ነጻ ካወጣቸው በኋ ነጻነታቸውን እንደፈለጉ እንዳይንሸራሸሩበት "ነጻ የወጣችሁት ለዐለማ ነው፤ ዐለማዉ ደግሞ የመጀመሪያው እኔ አምላክ አንድሆናችሁ፤ አናንተም ሕዝብ ትሆኑኝ ዘንድ ነው ብሎ ጉዳዩን በሲና ተራራ ሳሉ ነገራቸው። ታሪኩን ብታነቡት ሁሉም ከግብ ወጥተዋል፣ የተራራውን ግርጌ ይዘው መጥተው ቆመዋል፣ ወደ ተራራው ጫፍ ግን

አልወጡም።

ከግብፅ መውጣት እና ወደ ተራራው መቅረብ አንድ ደረጃ ቢሆንም፤ ወደ ተራራው ላይ መውጣት ግን ሌላ እርከን ለለሆነ ወደዚያ አልወጡም። አነዚህ ሕዝቦች በዘጸአት 24፣9-11 ላይ የወርቅ ጥጃ ሠርተው "እግዚአብሔር ይሄ ነው" ባሉ ጊዜ እግዚአብሔር አንዲህ አላቸው። *"ሙሴም፣ አሮንም፣ ናዳብም፣ አብዩድም፣ ከሰባቱም ሰባ ሽማግሌዎች ወጡ፤ የአስራኤልንም አምላክ አዩ፤ ከእግሩም በታች አንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ አንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበረ። አዘ'ንም በአስራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም አነርሱም እግዚአብሔርን አዩ፣ በሉም ጠጡም።"*

ይሄ ሁለተኛ ደረጃ ነው ሙሴ አሮንን፣ ናዳብን፣ አብዩድን፣ ሰባ ሽማግሌዎችን ይዞ የቆመው ከተራራው ግርጌ በታች ሳይሆን ትንሽ ወደ ተራራው ከፍ ብሎ ወጥቶ ነው። በዚያ ለፍራ ላይ እግዚአብሔር ተገናኝቸው። አነርሱም እግዚአብሔርን አዩ፤ ከእግሩ በታችም እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ፣ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበረ፤ አጁንም በአስራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም፤ አነርሱም እግዚአብሔርን አዩ።

ሰው እግዚአብሔርን አይቶ አንደማያውቅ እና ቢያየውም በሕይወትም እንያሣይኖር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘጸአት 33፣20፤ ዮሐንስ 1፣18)። ሰው እግዚአብሔርን አይቶ በህይወት አንደሚኖር እንዴት ተብሎ መግለጽ እንደሚቻል አላውቅም። ይሁንና ክፍሉ ግን እግዚአብሔርን አዩ ይለናል። ያሳያቸው የሚያበራ ወለል የሚመስለውን የሚያብረቀርቅ ከብሩን ነው። ከእግሩም በታች ተቀመጡ፤ እነዲያውም በሉ፣ ጠጡም ይላል። እግዚአብሔር ምን ይመስል ይሆን? በእግዚአብሔር ፊት፣ እግዚአብሔር ባለበት፣ መብላት መጠጣትስ!?

አነዚህ ከተራራው ግርጌ በታች ከቆሙት ከህዝቡ ይልቅ አንድ ደረጃ ወደ እግዚአብሔር የተጠጉ፣ ወደ ተራራው ላይ መውጣት እና ተራራውን መንካት ብቻም ሳይሆን ወጥተው እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ጉብተው የበሉ እና የጠጡም ናቸው።

ዘጸአት 24፣12-13 *"እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ አኔ ወደ ተራራው ውጣ፣ በዚያም ሁን፤ አንርሱን ታስተምር ዘንድ አኔ የጻፍሁትን ሕግና ትእዛዝ የድንጋይ ጽላት*

አሰጥሃለሁ አለው:: ሙሴና ሎሌው ኢያሱ ተነሡ፤ ሙሴም ወደ አግዚአብሔር ተራራ ወጣ"::

እዚህ ላይ ኢያሱን ማንሣት አፈልጋለሁ:: ሰባዎቹ የእሰራኤል ሽማግሌዎች፣ አሮንም፣ አሚናዳብም ሰማቸው የተጠቀሱት በሙሉ እዚያው የቦሉበት የጠጡበት ቦታ ሲቀሩ ኢያሱ ግን ከሙሴ ጋር አብሮ ወደ ላይ የተወሰነ መንገድ ተጉዟል:: እንዲያውም ሙሴ በሄደበት መንገድ፣ የመገናኛው ድንኳን በተንቀሳቀሰበት ቦታ፣ በዞረበት ቦታ አብሮ ሲዞርም ታገኙታላችሁ:: ሰው ሁሉ ወደ ማደሪያ ድንኳኑ ሲመለስ ኢያሱ ግን በመገናኛው ድንኳን በር ላይ ይቀመጥ፤ ከዚያም አይለይም ነበር::

አግዚአብሔር በሙሴ ፊንታ ሰው መተካት በፈለገ ጊዜ የመረጠው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እየገባ ያገለግለው የነበረውን ሊቀ ካህናቱን አሮንን ሳይሆን ኢያሱን ነበር:: ኢያሱን የተመረጠበት ምክንያት ወደ አግዚአብሔር የሚጠጋ ልብ፣ ሐሳብ እና በአግዚአብሔር መንገድ የመሄድ ፍላጎት ለለነበረው ነው:: ሁልጊዜ አግዚአብሔር ዋጋ በቆጠረለት በማደሪያ ድንኳኑ ደጃፍ ላይ የማይታጣ፣ ልቡ፣ ሐሳቡ በአግዚአብሔር ድንኳን እንዲያውም በራሱ በአግዚአብሔር ላይ የነበረ ለው በመሆኑ ነው:: ለባዎቹ ሽማግሌዎች፣ አሮን እና ልጆቹ ከተራራው ቢታች ሲቀሩ አርሱ ግን አንድ ደረጃ ወደ ላይ ከፍ ብሎ የወጣ ለው ነው::

በዘጸአት 24፥15-17 ላይ የተጠቀሰ አንድ ሌላም የሚበልጥ ክፍታ አለ:: *"ሙሴም ወደ ተራራ ወጣ፤ ደመናውም ተራራውን ሸፈነው:: የእግዚአብሔርም ክብር በሲና ተራራ ላይ ተቀመጠ፤ ደመናውም ሲድስት ቀን ሸፈነው፤ በሰባተኛውም ቀን ከደመናው ውስጥ መሴን ጠራው:: በተራራው ራስ ላይ በእስራኤል ልጆች ፊት የእግዚአብሔር ክብር መታየት እንደሚያስጥል አሳት ነበረ:: ሙሴም ወደ ደመናው ውስጥ ገባ ወደ ተራራውም ወጣ፤ ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀን አርባ ሌሊትም ቆየ"::*

ይሄኛው ደግሞ ሌላ ደረጃ ነው:: እንዴት የሚገርም ነገር ነው!! ከተራራው ቢታች ሁሉም እንድ ላይ ነበሩ:: አግዚአብሔርም ሙሴን ወለን ሊድርግላቸው እንዳይመጡ አለ:: ከዚያም ከአንተ ጋር ሰባ ሽማግሌዎች፣ አሮን እና ልጆቹ እንዲሁም ኢያሱ ይምጡ አለ:: በዚያም ከፍታ ላይ አውጥቶ አበላቸው፣ አጠጣቸው:: በመቀጠል ደግሞ ኢያሱ እና ሙሴ ብቻ የወጡበት አንድ ከፍታ መጣ:: በመጨረሻ ደግሞ ኢያሱ

ቀሮቶ ሙሴ ብቻውን የወጣበት ከፍታ ተገኘ::

ሙሴ ብቻውን ወደዚያ ከፍታ በወጣ ጊዜ ደመናው ለስድስት ቀን ሸፈነው:: የለብራውያን መልዕክት ጸሐፊ *"ሙሴም ሊሮግ ለፈራለሁ፥ እንቀጠቀጥማለሁ አለኪል ድረስ ዮሚታየው ሊሮግ ዮሚያስፈራ ነበረ" (ዕብራውያን 12፥21)* ብሎ እንደ ነገረን ሥጋ ለባሹ ሙሴ አርባ ቀን ሙሉ በአግዚአብሔር ፊት እንዴት መቆየት ቻለ? የአግዚአብሔር አሳት ሲወርድ እንዴት አያስፈራ፤ እንዴትስ አያንቀጠቅጥ!!

ይሁንና ጉዳዩ የፍቅር፣ የመጠጋጋት በመሆኑ አግዚአብሔር አስጠጋው:: አግዚአብሔር ይሆንን ሰው በራሉይ ወይም በሕልም ተገልጦ ሳይሆን አፍ ለአፍ ያናግረው እንደ ነበርም ተናግሯል (ዘኁልቁ 12፥7):: ይሄ እንዴት ያለ መጠጋጋት ነው!?

ይህ ሙሴ አርባ ቀን በአግዚአብሔር ፊት ቆይቶ ከተራራው ሲወርድ ፊቱ አበራ፤ አርሱ ግን ፊቱ ያበራ እንደ ነበር አያውቅም ነበር:: ለካስ ሰው ከልቡ ወደ አግዚአብሔር ከተጠጋ፣ ራሱን ለአግዚአብሔር ከሰጠ፣ አግዚአብሔርን ከወደደ፣ በነፍሱ፣ በሥጋው እና በመንፈሱ "ሮኻብ እና ጥማቱ ፊትህን፣ ክብርህን ማየት ነው" ካለ፣ ከአንድ መንፈሳዊ ደረጃ ከፍ ወዳለ ሌላ ደረጃ ይሸጋገራል:: እዎን ከፍ ብሎም ይወጣል!!

ወገኖቼ ሆይ! አርግጥ ነው ሁላችንም በአግዚአብሔር ጸጋ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም በዋጋ ተገዝተናል:: ይሁንና ሁላችንም እኩል አይደለንም:: እያንዳንዱን ሰው ወደዚህ ጌታ የመቅረብ የግል ትጋቱ፣ ጥማቱ እና መሰጠቱ ይለያየዋል:: ወደ አግዚአብሔር የመቅረብ ዕድሉ ለሁላችንም በእኩል ተሰጥቶናል:: ነገር ግን ሁላችን እኩል ስለማንቀርብ መለያየት እንዳለ ተገነዘባችሁልኝ? እኔ የትኛው ደረጃ ላይ ይሆን ያለሁት? እናንተስ?

እያችሁ ለለዎች ብር ሰጥታችሁ "በሉ አሁን እያንዳንዳችሁ የፈሊጋችሁትን ገዝታችሁ ተጠቀሙበት፤" ብትሏቸው እያንዳንዱ ሰው የሚገዛው ነገር ይለያያል:: የገነዘበ አወጣጣችን እንደ ፍላጎታችን የተለያየ እንደሆነ ሁሉ ሕይወታችንም እንደዚያው ነው:: ወደ አግዚአብሔር መቅረብን በተመለከተ በዚህ ምድር እንኖርበት ዘንድ የተሰጠንን ይህን ሰባ ወይም ለማንያ ዓመት ዕድሜያችንን የምንሰጠው እርሱን ያዘውነውን ያህል ነው:: እርሱን በብዙ ለማወቅ ከተሰጠን ብዙ እውቀትን ይሰጠናል:: "ነፀዳጂ እንዴት እደብቀዋለሁ?" በሚል የልቡን ገልጦ ወደሚነግርህ ሰው ልቡ ውስጥ

መግባት ይቻላል። ይሁንና አዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስ ግን ራስን ማስለመድ ይጠይቃል። ለዚህ የሚሆን አንድ የአዲስ ኪዳን ምሳሌን ላቅርብላችሁ።

ከርስቶስ እና ደቀ መዛሙርቱ የነበራቸውን ግንኙነት ብንመለከድ ይህንን እውነት ማየት እንችላለን። ጌታ በየደረጃው ሰዎች ነበሩት። መጽሐፍ ቅዱስ *"ከዚህ በኋላ ጌ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፣ ሁለት ሁለትም አድርጎ አርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ሰፍ ሁሉ በፊቱ ላካቸው" (ሉቃስ 10፥1)* እንደሚለን ከታምራቱ ሰለ በሉ እና ሰለ ጠበ ይከተሉት ከነበሩት ሕዝብ ተለይተው እና ተመርጠው የወጡ ደቀ መዝሙር ተብለ የሚታወቁት ሰብዓ ሰዎች ከሌላው ከብዙኀኑ ሕዝብ ለአርሱ የቀረቡ ነበሩ።

እነዚህ ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ። ጌታ ታማኝ ሆነ ስላኛቸው መልዕከተኛ ይሆኑት ዘንድ ዘይቱን በእጃቸው ላይ አድርጎ "ውጡ የታመመውትን ዘይት እያደረጋችሁ ፈውሱ፣ አጋንንትን አውጡ፣ ወንጌልን ስበኩ፣ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት እየዘራችሁ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች እያላችሁ አዋጁ ንገሩ" አላቸው። ይሄ አንዱ የቅርበት ደረጃ ነበር።

ሌላው ደግሞ መጽሐፍ *"በአንዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ ሌሊቱን ሁሉ ወደ አግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ ከአነርሱም ዐሥራ ሁለት መረጠ፤ ደግሞ ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤ አነርሱም፣ ጴጥሮ ብሎ አንደ ገና የሰየመው ሰምዖን፣ ወንድሙም አንድርያስ፣ ያዕቆብም፣ ዮሐንስም ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፣ ማቴዎስም፣ ቶማስም፣ የአልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፣ ቀናተኛ የሚባለው ሰምዖንም፣ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳም፣ አሳልፎ የሰጠውም የአስቆሮቱ ይሁ ናቸው" (ሉቃስ 6፥12-13)* አንደሚል ከሰባዎቹ ውስጥ መርጦ ሐዋርያት ብሎ እነዚህ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው።

ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት አንደ ደረሰ አውቆ፣ አርሱ ከዚህ ምድር ተለይቶ ሲሄድ ሥራውን በዐደራ የሚወጡ፣ አርሱ በሄደበት የመሰቀል መንገድ ሊሄዱ የቀረቡ፣ በሞቱ እንኳ አርሱን ሊመስሉት የጨከኑትን እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን *"ባሪያ ከጌታው አይበልጥም፤ መልዕከተኛም ከላከው አይበልጥም። ይህን ብታውቁ፣ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ" (ዮሐንስ 13፥16-17)፤ ". . .ከአንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፣ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለአናንተ አሰታውቄያችኋለሁና" (ዮሐንስ 15፥15)* አላቸው።

በቀላይ ያደረገውንም ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ እንዲህ በማለት ይነግረናል። *"እ.የሱስም በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።*

.ከአራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፣ ማበሻም ጨርቅ ወሰዶ ታጠቀ፣ በኋላም ለሎ.ታጠቢያው ውኃ ጨመረ፣ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨ.ርቅ ሊያብስ ጀመረ" (ዮሐንስ 13፥4-5)።

እነዚህ ከሰባዎቹ ተመርጠው የተሾሙት ዐሥራ ሁለቱ ደግሞ ናቸው። የሚገርም ነገር ነው። የኢየሱስ ንግግር አንጀት ይበላል። በዚያን ወቅት ጌታ ኢየሱስ በሚያነሰግልበት ጉባኤ ላይ ቁጥራቸው ከ1000 እስከ 6000 የሚሆን ህዝብ ይኖኝ አንደ ነበር ይገመታል። እንግዲህ ከእነዚህ መካከል በመጀመሪያ ሰባ፣ ቀጠለና ከሰባዎቹ ዐሥራ ሁለቱን፣ ከዐሥራ ሁለቱ መካከል ደግሞ ሦሱቱን መርጦ ወሰዶ በተራራው ላይ ከብሩን ገለጠላቸው።

እነዚህ ወደ ደብረ ታቦር ተራራ ላይ ወሰዶ ክብሩን ገልጦ ያሳያቸው ሦስት ደቀ መዛሙርትም ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና የሐንስ የተባሉት ናቸው። *"ከሰዱስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን አና ያዕቆብን ወንድሙንም የሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው፣ በፊታቸውም ተለወጠ፤ ፊቱም አንደ ጸሓይ በራ፣ ልብሱም አንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። አነሆም፣ ሙሴ እና ኤልያስ ከአርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። . . ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ፡- የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ሰማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው" (ማቴዎስ 17፥1)።*

እነዚህ ሦስቱ ውልጊዜ ስማቸው አንድ ላይ ነው የሚጠራው። *"ወደ ቤትም ሲገባ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ከዮሐንስም ከብላቴናይቱም አባትና እናት በቀር ማንም ከአርሱ ጋር ይገባ ዘንድ አልፈቀደም" (ሉቃስ 8፥51)።*

ጌታ በኢያኢሮስ ቤት ውስጥ ልጅቷን ከሞት ሲያስነሣት ሲሄድ ዐሥራ ሁለቱ ይግባም ሰብዓዎቹ ተከትለው መጥተው ነበር። እናም ልክ ልቅሶ ቤቱ እንደ ደረሰ ከእኔ ጋር ወደ ቤት ውስጥ መግባት የሚችሉት እነዚህ ሦስቱ እና የልጅቷ አናትና አባት ብቻ ናቸው አለ። ከዚያም በትንሣኤው ጌታ ሞት የያዘውን ምርኮ ሲለቅ፣ ትዋቋን ሲፈታ፣ ለእግዚአብሔር ልጅ ድምፅ ሲታዘዝ እና ለቀብር ተዘጋጅታ የነበረችው ብላቴና እንደገና ሕያውት ዘርታ ስትነሣ እና ቆማ ሰትሄድ ያዩት ሦስቱ ናቸው።

እያችሁ፣ እግዚአብሔር እብ ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት የሰሙት፣ የሕ እና የነቢያቱ ተምሳሌት የሆኑትን ሙሴን እና ኤልያስን ያዩዋቸው እንዲሁም ገ "ያያችሁትን ለማንም እንዳትነግሩ" ያላቸው፣ እነዚህ ደቀ መዛሙርት የወጡበት ይህኛ ደረጃ እንደ ሰብዓዎቹ፣ እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሳይሆን ወደ እርሱ የተጠጉ፣ ልቡ ውሪ የገቡ ስለነበሩ ነው። ወደ ጌታ የመጠጋት ጉዳይ እንዴት የተወደደ እና የከበረ ነገር ነው

እምን! ሁላችንም በጌታ ፊት በተመሳሳይ ደረጃ ላይ አይደለም ያለነው ሁላችንም የትኛው ደረጃ ላይ እንደምንገኝ የሚያውቀውም እግዚአብሔር ብቻ ነው *"እንዳንዶች ቤተ መቅደሱ በመልካም ድንጋይ እና በተሰጠው ሽልማት እንዳጌጠ ባዩ ; ሲነጋገሩ ሰምቶ ይህ የምታዩት ሁሉ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀር ዘመን ይመጣል አላቸው" (ሉቃስ 21፥5)።* እነርሱ (ደቀ መዛሙርቱ) ግን ይሄ መ ይሆናል? የሚል ተመሳሳይ ጥያቄ ስለነበራቸው *". . .መምህር ሆይ እንግዲህ ይህ መ ይሆናል? ይህስ ይሆን ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድነው? ብለው በጠየቁት ; እንዲህ አሉአቸው። እንዳትስቱ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች . .በስሜ ይመጣሉና፤ እነርሱ ተከትላችሁ አትሂዱ። ጦርንና ሁከትንም በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ አስቀደ ይሆን ዘንድ ግድ ነውና፤ ነገር ግን መጨረሻው ወዲያው አይሆንም" (ሉቃስ 21፥5-* ሲል ለብቻቸው ነግሯቸዋል። ቸር እምላክ ለእኛ ደግ ሆኖ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው በመጽሐፍ አስጽፎ ላጠን እንጂ ይሄ እኮ ለእነርሱ ብቻ የተነገረ ምስጢር ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ፣ ትጋ" የሚለ ቃል እና ይህ ልምምድ፣ አንድ ጊዜ ተጀምሮ ከዚያ በኋላ በራሱ ቁልቁለት እየተምዘገ እንደሚወርድ ጎማ አይደለምና፣ እግዚአብሔርን መምሰል ከእኔ እና ከእናንተ የሚጠበ ድርሻችን ስለሆነ እርሱን ለመምሰል እንሩጥ! እንትጋ!

ሐዋርያው ጳውሎስ *"እርሱን እና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ . .፣ እን ነገር ሊደርጋለሁ፣ በኋላዬ ያለውን ለየረሳሁ፣ በፊቴ ያለውን ለመያዝ አዘረጋለሁ (ፊልጵስዩስ 3፥10-13)* እንዳለው ቀንም ሆነ ሌሊት እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ እ እርሱን ወደ መውደድ ውስጥ እንባ ዘንድ ራሳችንን እንስጥ።

ከእነዚህ ከሦስቱ ደግሞ አብልጦ ወደ ጌታ የሚጠጋ አንድ ደቀ መዝሙ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ደቀ መዝሙር ማን እንደሆነ ስሙን ባይጠቅሰውም የሐን በወንጌሉ ሲናገር *"ኢየሱስ ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ*

ተጠጋ" (ዮሐንስ 13፥24) ይለናል። እርግጥ ነው ኢየሱስ ሁሉንም ይወዳቸው ነበር፤ ነገር ግን ይሄኛውን ደቀ መዝሙር ለብቻው ለይቶ ይወደው ነበረ። ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ለመግባት፣ ለመጠጋጋት እርሱን በማወቅ የቀረበ ትሥሥር ይኖረን ዘንድ ምን ማድረግ አለብን? በመቀጠል ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ የምንማራቸውን አራት ነገሮችን ብቻ ልንገራችሁ።

፩. የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር መውደድን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕድሜው 12 ዓመት በሆነ ጊዜ ከእናቱ ጋር ወደ እየሩሳሌም ሄዶ ነበር። በዚያ ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላም ሲመለሱ እርሱ ግን በኢየሩሳሌም ቀረ። ዮሴፍ እና ማርያም ግን በዚያ መቅረቱን አላወቁም ነበር። ከመንገደኞች ጋር እየመጣ መስሏቸው ትተውት ሄዱ። በኋላ ተመልሰ አሰመምጣቱን ሲያውቁ፣ እንደገና ተመልሰው ፍለጋ ሄዱ። እናም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተቀምጦ ከሕግ መምህራኑ ሲሰማ እና ሲጠይቃቸው አገኙት። እናቱም "ልጄ ሆይ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ አባትህ እና እኔ እየተጨነቅን ለንፈልግህ ነበርን" ስትለው እንዲህ ሲል ነበር የመለሰላት። "ስለ ምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት አሆን ዘንድ እንዲገባኝ አታውቁምን?" (ሉቃስ 2፥41-49)።

ወገኖቼ ከእርሱ ሕይወት እንማር። ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ለመጠጋት እግዚአብሔርን እና የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር እንውደድ። ግድ የላችሁም ደጁን እንውደድ፣ ሕዝቡን እንውደድ፣ የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ እንውደድ፤ የእግዚአብሔርን መቅደስ ስትፈሩ እግዚአብሔርን ትፈሩታላችሁ፤ የእግዚአብሔር መቅደስ ሲናፍቃችሁ እግዚአብሔር ይናፍቃችኋል። *"እቤቱ፣ ርዳታው ከለንሶ ዘንድ የሆነለት፣ በልቡም የሚይኖውን መንገድ የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው" መዝሙር (84)፥5* ብሎ የዘመረው ዘማሪ አደባባዮችህን ወደድኳቸው ብሎ ነበር። ቃሉ ወደሚነገርበት፣ ስሙ ወደሚመሰገንበት የእግዚአብሔር ፍቅር እና ሞገሱ በሕዝቡ ላይ ወደሚፈሰበት ወደ እግዚአብሔር ቤት መምጣትን ውደዱ።

በዚህ ከተስማማን እንግዲያው ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ለመግባት የምንለማመደው የመጀመሪያው ነገር ምንድነው? የእግዚአብሔርን ቤት፣ የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር መውደድን ነው። ልብ በሉ! ኢያሱ ዘወትር ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አጠገብ የማይታጣ ሰው ነበር።

2. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ

ከኢየሱስ የምንማረው ሌላው አንድ ምስጢር የሚከተለው ነው። አንድ ጊዜ ጌታ ብዙ ሰዎች በዙሪያው ተቀምጠው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል እያስተማረ ሳለ፣ እናቱ እና ወንድሞቹ መጡና በውጭ ቆመው አስጠሩት። የተላኩትም ሰዎች "እነሆ እናትህ እና ወንድሞችህ በውጭ ቆመው ይፈልጉሃል" አሉት። እርሱ ግን "እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? . . እነሆ እናቴ እና ወንድሞቼ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው፤ እናቴም እህቴም አላቸው (ማርቆስ 3፣35)።

የወንጌሉ ጸሐፊው ስለዚህ ላይ ለየነገረን ያለው ጌታ እናቱን እና ወንድሞቹን እየካደ እንደሆነ አይደለም። ምስጢሩ እግዚአብሔርን ውደዱ፣ ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ግቡ፣ ወደ እርሱ ተጠጉ እና ፈቃዱን አድርጉ፤ ይህን ከእኔ ሕይወት ተማሩ የሚል ነው። አንድ ጊዜ ጌታ ራሱ "እኔ ደስ የሚያሰኘውን ስለማደርግ አብ ብቻዬን አይተወኝም" አለ። ሁልጊዜ "ፈቃደህ ነው ወይ?" ብሎ አብ የሚወደውን ብቻ ተግቶ ያደርግ ነበር።

ወገኖቼ ሆይ! እግዚአብሔር ማስተዋሉን ይስጠን። የፈለግነውን ነገር አድርገን "እርሱ ይህን እና ያንን ማድረግ እንደማልችለው፣ አንዳቃተኝ ችግሬን ያውቀዋል፤ ምንም ችግር የለውም" እያልን ስንት ጊዜ በድፍረት ሄደናል መሰላችሁ። አውነት ነው ጌታ ያለንበትን ያውቃል። ነገር ግን እግዚአብሔር ሌላ ምርጫ የለውም፤ ፈቃዱን እናደርግ ዘንድ ብቻ ነው የሚፈልገው። ስለዚህ እግዚአብሔርን መውደድ የምንለማመድበት አንዱ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል መማር፣ ማወቅ፣ እና ያወቅነውንም በተግባር በመታዘዝ መለማመድ በመሆኑ፤ በዚህም እግዚአብሔርን ከመውደድ አንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ መሸጋገር እንችላለን።

3. ስለ እግዚአብሔር ቤት መቅናትን

አሁንም ከጌታ ሕይወት የምንማረው አንድ ዐቢይ ጉዳይ አለ። ዮሐንስ በወንጌሉ *"የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር፣ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በመቅደስም በፈዎችንና በሳንቲ ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አየ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም፣ በፈዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፤ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ፤ ገበታዎቻቸውን ገለበጠ፤ ርግብ ሻጪዎችንም፦ ይህን ከዚህ ውሰዱ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው" (ዮሐንስ 2፣13)* ሲል

ይነግረናል።

ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ሰዎች በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይሸጣሉ፣ ይለውጣሉ፤ ጫጫታው እና ግርግሩ ሲታይ እንኳንስ የሚባላ አሳት የሆነው ቅዱሱ እግዚአብሔር ቀርቶ የሰው አስተዳዳሪ ያለበት ስፍራም አይመስልም ነበር። በዚያን ጊዜ ጌታ ጅራፉን እነሣ። ከዚያም ሻጭ እና ለዋጮቹን በጅራፍ መግረፍ፣ ሸቀጣቸውንም መገልበጥ ሲጀምር ወፎቹ መብረር ጀመሩ፣ ገንዘቡም ተበታተነ። ሰዎቹም ከጅራፉ ሰማምለጥ መሮጥ፣ መራኮት ጀመሩ። ያስፈራል!!

እግዚአብሔር አሳቱን እንዲጥል ብዙጊዜ ለምንንዋል አይደል? አዎን አሳቱን ሁልጊዜ እንናፍቃለን፤ አናንተ እንደምትጠሙት እኔም አጠማዋለሁ። ሁሌም የምጸልየው ጸሎት ነው። ነገር ግን ልቤ የሚፈራው ነገር አለ። አያችሁ ይህ አሳት እንደሚቀድሰን ሁሉ የሚፈርድብን፣ እንደሚባርከን ሁሉ የሚቀርጠንም አለን። አናም ጌታ ምን አለ? "የቤትህ ቅናት ይበላኛል" ብሎ ጮኸ። ሁሉንም ነገር ገለባበጠው።

እግዚአብሔርን መውደድ የምንለማመድበት አንዱ ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር እና ቅንዓት ከውስጣችን ሲመጣ ነው። ከውስጣችሁ የሚነሣውን ስለ እግዚአብሔር የሆነውን ቅንዓት አና የእግዚአብሔርን ፍቅር አናፍነው፣ አንጣለው፣ አንረጋግጠው፣ በሦስኝታ አናሳልፈው። ይህንን ቅንዓት ቅዱስ በሆነ መንገድ ልንይዘው ይገባል።

አያችሁ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጡ ቅንዓት ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ባል ሚስቱን "እኔ በጣም ነው የምወድሽ ግን ቅናት የሚባል ነገር የለኝም" ካለ ልትሰቀበት ትችላላችሁ። ምክንያቱም ንጹሕ ፍቅር በውስጡ ጥላቻ የለውም። ይሁንና ስው ግን ላፈቀረው ቅንዓት ሊኖረው ይገባል።

እግዚአብሔርን መውደዳችን ዓለምን እንድንጠላ ያደርገናል። አግዚአብሔርን መውደድ ለእግዚአብሔር ቤት እንድንቀና ያደርገናል። ይሄ ከሌለበትና "እንዲትም ብፈስ ግድ የለኝም" ከሆነ ነገሩ አርሱ ፍቅር አይደለም። በጌታ ሕይወት ውስጥ የሆነው ይህ ነው። ስለዚህ ይህን ዓለም እና ከዓለም የሆነውን ነገር መጥላት፣ አምቢኝ ማለት መለማመድ ይገባናል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆነ የእግዚአብሔር ስው "ይህ የዚህ ዘመን ትውልድ እግዚአብሔርን በዜማ ሲያመልከ ስመለከት ነፍሴ ደስ ይላታል። ሐሴትም

አደርጋለሁ። ይሁን እንጂ በውስጡ የዓለምን ነገር መጥላት ይኖረው ይሆን ወይ? ብዬ ሳስብ አፈራሁሁ" ሊል ተናግሮ ነበር። ይህ መጋቢ ሊገልጸው የፈለገው ዓለምን መጥላት ምን ዐይነት ጥላቻ ይሆን? ርኩሰን ነገር የመጠየፍ፣ የሰይጣን የሆነውን፣ ዐመፅ ያሰበትን ነገር የመጥላትን ጥላቻ ነው። ጌታ እባቱን የወደደበት ፍቅር በውስጡ ቆራጥ ርምጃ ሰመውሰድ የወሰነበት ቅንዓት ነበረው። እኛም ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የእግዚአብሔርን፣ የእግዚአብሔር ካልሆነው ነገር ከመጠየፍ እና ከመጥላት ጋር ሊጣመር ይገባል።

4. ፈተናን በጽናት ማለፍን

ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚቦረብሩ ነገሮች ስለሚመጡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ፈተናን በጽናት ማለፍን መሰማመድ ያስፈልጋል። የሚፈትሸን ነገር ሲመጣ እምቢኝ እያልን መሄድ ይኖርብናል። በትዳር ውስጥ ሚስት ወይም ባል ከሁለት አንዳቸው በውጪ ባላቸው ግንኙነት ወደ ፈተና የሚያስገባቸው ነገር ሊኖር፣ ፍቅራቸው አንዲጠነክር ካሰፈለገ ፈተናዎቻቸውን በሙሉ "እምቢኝ" የሚሉ መሆን አለባቸው።

ለዚህ ነው ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን ሊፈትነው በመጣ ጊዜ ጌታ "ሰው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው የሚኖረው፤ ለጌታ ለአምላክ ብቻ ስገድ ተብሏል፤ አምላክህን አትፈታተን" ተብሏል እያለ ደጋግሞ እየነገረው ለእባቱ ሰለእግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት ያሳየው። ጌታ ወደ መሰቀሉ ያመራው ለሶ *"ነገር ግን አብን እንደወደድ ዓለም ሊያውቅ፣ አብም እንዳዘዘኝ፣ እንዲሁ አደርጋለሁ። ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ" (ዮሐንስ 14፡31)* ብሎ ነው።

ፈተና ሲመጣ አምቢኝ ብሎ ጸንቶ መቆምን እንድንለማመድ የሚያደርገን ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ነው። በዚህ ዘመን ሰው ከፈተና እና ከመሰቀሉ እየሸሸ እየኖረ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለት አይችልም። የእግዚአብሔርን ፍቅር መሰማመድ የምንችሰው ፍቅሩ ከሌላ ቦታ መጥቶልን አይደለም። ገና ወደ ጌታ በመጣን ጊዜ በልባችን ውስጥ የፈሰሰውን የጌታን ፍቅር ልናስበው ይገባል።

ኤፌሶን መልዕክት ምዕራፍ 6:24 *"ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን ለሚን"* ይላል። ባለመጥፋት ማለት ምን ማለት ነው? ኢየሱስን በማያቋርጥ ፍቅር ለሚወዱ ሰዎች ጸጋ እና ሰላም ይሁንላቸው ማለትስ ምን

ማለት ነው? ከዛሬ ስንት እና ስንት ዓመታት በፊት የተቀበላችሁትን ያንኑ ጌታ ዛሬም በዚያው ጥልቀት እና ክብደት፣ በዚያው ፍቅር እና ወዳጅነት መውደድ ማለት ነው። ጌሥ ከዓለም፣ ከንዝብ፣ ከተቃራኒ ጾታ ፍቅር፣ በዓለም ከሚገኘው ከብር እና ዝና ይልቅ እነኑ ትበልጥብኛለህ የምንለውን ዐይነት ፍቅር ይፈልገዋል። ፍተሻው ያለው አዚህ ውስጥ ነው።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2 ላይ ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን ከመረመራት በኋላ እንዲህ አለት *"ዳሩ ግን የምንቅፍብህ ነገር አለኝ ሥራህንም ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ፤ ንስሐም ግባ ሥራህንም ሥራሀን አድርግ፤ አለዚያ ለመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው አወስዳለሁ"*።

የክርስትና ሕይወትን ጉዞ ስንጀምር ዘምረን፣ ጸልዮን፣ የጌታን ልጆች ስናገኝ ተሳስመን፣ ስለ ጌታ አዳኝነት ለሰዎች መስከረን የማእጠግብበት ሰጌታ የነበረን የቀደመ ፍቅር፣ የወንጌል አሳት እና የልብ መቃጠል የት ነው ያለው? ዘንድሮ ተትትጉተንም ቢሆን ስለ ጌታ ለመናገር አፋችንም እጃችንም እምቢ ብሎናል። ያ የመጀመሪያ ፍቅራችን የት ገባ? ትንሽ ወደ ኋላ ልውሰዳችሁ።

አንድ ወቅት ላይ ሌዊ የተባለውን ልጄን አገር ቤት አዲስ አበባ ይገፎው ሄጀ ነበር። "የት ልውሰደው?" ብዬ ሳስብ፤ ድሮ ልጅ እያለሁ ያደኩበት ሰፈር ትዝ አለኝ። እናም ዕድሜዬ ምናልባትም ሦስት ወይም አራት ዓመት ከነበረበት ዘመን ጀምሮ ወደ ሞርኩበት ቤት ወሰድኩት። ከዚያም ጌታን በተቀበልኩበት ወራት እሄድባት ወደነበረች ቤተ ክርስቲያን፣ ከሰኞ እስከ አርብ በየቀኑ ምሳ ሰዓት ላይ አቀመጥበት፣ እጸልይበት ወደነበረበት ሁሉ ወስጀ አሳየሁት።

ከሰፈር ልጆች ጋር ዝም ብሰን ተያይዘን ሄደን እንቆምበት የነበረውን የሰፈራችንን መግቢያ እና መውጫ በሩን ሁሉ አሳየሁት። አሳይቼው እንደጨረስኩ ግን በውስጤ የሆነ ነገር ተፈጠረ። ጌታ እኔን ሲያገኘኝ የነበርኩበት ሁኔታ ትዝ አለኝ። አስደናቂ፣ ልብ ኮርኳሪ እና ስሜት ሰርሳሪ ትዝታ ነበር!

ወንኖቼ ሆይ ጌታ የት ስፍራ ነው ያገኛችሁ? አሰቲ ትዝ ይበላችሁ። ጉድጓድ አፋፉ ላይ ሆናችሁ ነበርን? በሰዎች ሁሉ ተገፍታችሁ ተጥላችሁ ነው? በደም

ተጨማሪቃችሁ ነው? በሱስ አስራት ታስራችሁ ነው? ወይስ ብቻችሁን በጨለማ ውስጥ በጭንቀት ተይዛችሁ ነበር? የት ነው ያገኛችሁ? እርግጠኛ ነኝ ሁላችንም ጌታ ሲያገኘን አሁን እንዳለነው አልነበርንም። ከዚያ የጭንቀት እና የመከራ አዘቅት ውስጥ አውጥቶን፣ በደሙ አጥቦ እንጽቶን፣ ልጅ መሄድ በሚገባው መንገድ ላይ እንሄድ ዘንድ እየመራን እና እያስተማረን፣ ቀን ከሌሊት እየጠበቀን፣ መልካም ፍቅሩ ሳይጓደልብን እዚህ አድርሶናል። አሁን የእርሱ ጥያቄ "ልጄ ሆይ በዚያው የመጀመሪያ ፍቅርህ ትወደኛለህ ወይ?" የሚል ነው።

ምዕራፍ 3

ለብቻችሁ በፀጥታ በእግዚአብሔር ፊት እረፉ!

ምዕራፍ ሦስት

ለብቻችሁ በፀጥታ በእግዚአብሔር ፊት እረፉ!

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአሜሪካ አገር በሙዚቃው ዓለም ዝነኛ የነበረ ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ኤልቪስ ፕሬስሊ የሚባል ዘፋኝ ነበር። ይህ ብዙ አድናቂዎች፣ አሞ:ሸሾች፣ ተከታዮች፣ አፋሽ አከንፋሾች የነበሩት ዘፋኝ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለያ: ብዙ ሰው ነበር የደነገጠው። ኤልቪስ ከተካነበት ዘፈን የማቀንቀን ከፍተኛ ችሎታ አና ተሰጥዖው የተነሳ አድናቂዎቹ ከነበሩት ከብዙዎች መካከል ጀኔሲስ ዋይስ የተባለ አንድ ወጣት ኤልቪስን ለመምሰል የማያደርገው ጥረት እና ግረት አልነበረም።

ዋይስ ቁርጥ ኤልቪስን ለመምሰል ያደርግ የነበረው ጥረቱን የጀመረው ፅጮጌው ገና አምስት ዓመት ሳለ ነበር። ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ ልክ እንደ ኤልቪስ ሁሉቱን የሸሚዝ ቁልፎች ክፍት አድርጎ ደረቱን እያሳየ ነበር የሚሄደው። አስተማሪዎቹ ከፋል ውስጥ የሸሚዝ ቁልፎቹን ፈትቶ ደረቱን ገልጦ ባገኙት ቁጥር ሁልጊዜ ይቀጡት ነበር። መምህራኑ ሲያዩት ይቆልፈዋል፤ ዘወር ሲሉለት ደግሞ መልሶ ይከፍተዋል። ዋ:ስ ይህን ሁሉ የሚሆነው ማንን ለመምሰል ነው? ኤልቪስን!

ከዚህም ሌላ የመኝታ ክፍሉ ግድግዳ በሙሉ በኤልቪስ ፎቶ የተሸፈነ ነበር። ትራስ ጨርቁ ላይ ሳይቀር የኤልቪስን ፎቶግራፍ አሳትሟል። ዋይስ ኤልቪስን ይህን ያህል ይወደው እና ያደንቀው ስለነበር አድጎ አቅም ሲያገኝ ቁርጥ ኤልቪስን ለመምሰል ሲል ፊቱን በቀዶ ጥገና አስለወጠ። ኤልቪስ የሙዚቃ ትርዒቱን በሚያቀርብ ጊዜ ነጭ ሜጣ አድርጎ ካየው ዋይስ ጥራት ያለው ሆነም፣ አልሆነም ነጭ ጫማ ገዝቶ ያደርግ ነበር። ኤልቪስ ያደረገውና ይህ ወጣት ያላደረገው አንድም ነገር አልነበረም።

ይህን ሁኔታውን የተመለከቱ የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች አንድ ወቅት ላይ በቴሌቪዥን ፕሮግራማቸው ላይ በእንግድነት ጋብዘው ላደረጉለት ቃለ መጠይቅ ለመልስም ኤልቪስን በጣም እንደሚያደንቀው እና እርሱን መምሰል እንደሚፈልግም

ነበር የገለጻላቸው። ኤልቪስን ከመውደዱ የተነሣ እርሱ በማይረዳቸው ቋንቋዎች የተጻፉ እንኳ ቢሆንም ኤልቪስን የሚያወድሱትን ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችን እና ፊልሞችን ይዙ ነበር።

ይህ ወጣት እንዲህ እርሱን ለመምሰል እንቅልፍ ያጣለትን፣ ፊቱን በቀዶ ጥገና አስከማስቀየር የደረሰለትን ሰው ኤልቪስን በአድሜ ዘመኑ ያየው እራት ጊዜ ያህል ብቻ ነበር።

እርሱንም ኤልቪስ ሁልጊዜ በጠባቂዎቹ የተከበበ ስለ ነበር ከርቀት እንጂ ፈጽሞ በቅርበት እንኳን ሊያየው አልቻለም። ይህ ወጣት ኤልቪስን በቅርበት ሳያየው ሆነ ሳያነጋግረው አውቄ ዘፋኝ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ይህ ወጣት ኤልቪስን ለመምሰል ይሆን ያህል በመትጋቱ የኋላ ኋላ አንዳንድ የፊልም ኩባንያዎች እርሱን የሚመስል ነገር አያዩ ሲመጡ የኤልቪስን ታሪክ በፊልም መስራት ሲፈልጉ ገንዘብ እየከፈሉት ኤልቪስን መስሎ እንዲሰራላቸው ያደርጉ ነበር።

ይህን ሰው ለመምሰል ይሄን ያህል ይተጋ የነበረው ይህ ወጣት እንዴት የሚገርም ልጅ ነው! ከልጅነቱ እንስቶ እስከ ጎልማሳነት ዕድሜው ድረስ ያውም ተጠግቶ ማየት ያልቻለውን እና ፈጽሞ ሊመሰለው የማይችለውን ሰው ፊቱን በቀዶ ጥገና አስቀይሮ በሁሉ ነገሩ እርሱን ለመምሰል የሚተጋ ከሆነ፣ እኛማ በቅርበት ሳይሆን በልባችን ውስጥ አብሮን የሚኖረውን እና "እኔን ምሰሉ" ያለውን ጌታ ለመምሰል ምን ያህል ልንተጋ ያስፈልገን ይሆን?

የአግዚአብሔር ቃል ሲናገር *"ጌርሱን እንደምንመስል እናውቃለን"* ይላል (፩ ዮሐንስ 3፡2)። ያኛው ምናልባት ቢሳካለት በምድር ለጥቂት ይጠቅም ይሆናል። አግዚአብሔርን ለመምሰል በምናደርገው በዚህ ልምምድ እርሱን ሰንመስል ግን ለአሁኑ ሕይወትም ሆነ ለሚመጣውም የሚጠቅመን ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር የኢየሱስን ሙሉ ሕይወት በመውሰድ እርሱ ይናገረው እንደ ነበረው ስንናገር፣ ያደርግ እንደ ነበረው ስናደርግ ጌታን እንመስላለን። ይሄ ደግሞ ትልቅ ልምምድ ነው። የአግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ የሚለን ልክ እትሌቶች ከፊታቸው ለሚጠብቃቸው ውድድር ለውነታቸውን እየገሩ

እንደሚያስለምዱት ሁሉ እኛም እንደዚሁ ኢየሱስን ለመምሰል ራሳችንን እንድናስለምድ ነው። ኢየሱስን በምን፣ በምን ልንመስለው እንደሚገባን ሁሉንም ነገሮች መዘርዘር ባያስፈልም ጥቂቱን ግን እንመልከት።

አንዳንድ አስተማሪዎች እነዚህን ልምምዶች በልብ ውስጥ የሚደረጉ እና በውጫዊ የምንሳተፍባቸው ልምምዶች በማለት ለሁለት ሲከፍሏቸው፣ ሌሎች ደግሞ የማንሳተፍባቸው ልምምዶች ይሏቸዋል። ይሁንና እኔ ግን አልከፋፍለውም። አንባቢያን ትረዱት ዘንድ እመቺ እንዲሆን ከላይ ጥቂት ነገሮችን አሳይቻለሁ።

እንደምታስታውሱት ቀደም ባለው ክፍል ላይ የተመለከትነው ስለ ቅርብ ግንኙነት፣ የጠበቀ አውቀት እና ወደ አግዚአብሔር ስለ መጠጋት ነበር። ያንን ለማድረግ ወሳኝ አግዚአብሔር ቤት መሄድን ማዘውተር፣ የአግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ መለማመድ፣ ለአግዚአብሔር ፍቅር መቅናት በአግዚአብሔር ፍቅር መጽናት ስንጀምር ከአግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ እንጀምራለን። እንደ አብርሃምም የአግዚአብሔር ወዳጅ መባል ደረጃ ያደርሰናል። በመቀጠል ሁለተኛውን ሐሳብ እነመልከት።

ይህም የምንመለከተው ሐሳብ በጸጥታ እና ለብቻችን ስለ መሆን (Silent and solitude) ይሆናል። ይሄ ነገር ለሕይወታችን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ነው የማምነው። ሂዱ ወስደው ለብቻቸው መሆን የማይችሉ ሰዎችን አይታችሁ ታውቃላችሁ? እነዚህ ሰዎች የሆነ የፍርሃት ስሜት የተቆጣጠራቸው፣ ሁልጊዜ በሰዎች መከበብን የሚፈልጉ፣ አንዳች ነገር ወይም የሰው ድምፅ ካልሰሙ እንድ ከፍል ውስጥ በር ዘግተው ብቻቸውን መቀመጥ የማይችሉ ናቸው።

ሁልጊዜ አጠገባቸው ለው እንዳይጠፋ ወይም የጫጫታ ድምፅ መስማት የሚፈልጉ፣ ቤታቸው ሲገቡ ቤቱ ዘሎ የሚውጣቸው ይመስል ቶሎ ብለው መዝሙር፣ ራድዮ ወይም ቴሌቪዥን ከፍተው ብቻቸውን እንዳይደሉ እንዲሰማቸው ድምፁን ከፍ አድርገው በማስጮህ ሲሰሙ የሚረጋጉ፣ ልክ አዲስ አበባ መርካቶ ገበያ አካባቢ እንደሚኖሩ ሰዎች የግርግር ሕይወት የተዋሃዳቸው ስንት ሰዎችን ታውቃችሁ? እምን፣ ሁልጊዜ ይህን በመሰለ ጩኸት እና ግርግር ውስጥ መኖርን የሚመርጡ ሰዎች አሉ። ይሄ እግዚአብሔርን እየመሰልን ለመሄድ በምናደርገው የከርስትና ሕይወት አካሄዳችን ውስጥ የሚያነቅፍ ከባድ በሽታ ነው።

ሰይጣን የእኔን እና የአናንተን ሕይወት ኢየሱስን በመምሰል ወደ እግዚአብሔር
ሙሉት ለመግባት ራሳችንን እንዳናስለምድ እንቆ የሚይዝባቸው እና ሰው ሁሉ በቀላ
የሚቀበላቸው ሦስት ዓይነት መሳሪያዎች አሉት። እንዱ ቅድም ያልኳችሁ ነው።
ሁልጊዜ ድምፅ፣ ጫጫታ እንዲኖር ማድረግ ነው። ሁለተኛው ሁልጊዜ በሰዎች እና
በሰዎች መካከል ግርግር እና ትርምስ መፍጠር ነው። ሦስተኛው ጥድፊያ ነው። ሰይጣን
ነፍሳችን ምንም ዓይነት የፀጥታ፣ የአረፍት እና የአፎይታ ጊዜ እንዳይኖራት ለማድረግ
ሕይወታችንን ሁልጊዜ የሚያመሰቃቅለው ድምፅ እንዲኖር በማድረግ ነው።

ይህን የአሁኑን ወጣት ትውልድ ልብ ብላችሁ አዩት። ስታዩት ምን
ይሰማችኋል? አታዝኑለትም!? "ለምን?" ቢባል አረፍት የለውማ!! ምን ዕረፍት አለው?
ከየትኛውም የሰውነት ከፍላቸው ይልቅ ብዙ ሥራ የሚሰራው አውራ ጣታቸው ነው።
በአውራ ጣታቸው ቴክስት ያደርጋሉ። በዚያ ላይ ጆሯቸው ውስጥ የማዳመጫ መሳሪያ
ወትፈው የፈለጉትን እየሰሙ ነው። መኪና ውስጥ ዘለው ሲገቡ የመኪናውን ሬዲዮ
ወይም ቴፕ ከመቼው እንደ ከፈቱት አይታወቅም። ፀጥታ ያስበረግጋቸዋል፤ ይፈራሉ።
አናም ብቻ አንዳች የሚያንባርቅ ድምፅ ይፈልጋሉ። በቤት ውስጥ፣ በመንገድ ላይ፣
በመስሪያ ቤት ወደ ውስጣቸው ዘልቆ የሚገባ አንዳች ድምፅ ይሻሉ። አበስኩ፤ ገበርኩ
ያሰኛል! "ጫጫታ የለመደ ሰው አባይ ወንዝ ዳር ቅበሩኝ" ይላል የተባለው ያለ ምክንያት
አይደለም ማለት ነው!?

ሰይጣን በሁሉ ቦታ፣ በማንኛውም ሰዓት ድምፅ እንዲኖር በማድረግ ሕይወት
ያለ አንዳች ድምፅ ፋይዳ የሌላት፣ ከቶውኑም ከአንቅስቃሴ ታግታ የታቀበች ዓይነት
እስመስሎ በማቅረብ ሰው ሁሉ ያንን ድምፅ አየሰማ አንዲባክን በግርግር አፍዝ፣
አደንግዝ ተቀፍድዶ እንዲኖር አድርጓል። ሰው የፀጥታ ሰዓት የለውም፤ ወደ ውስጥ
ራስን ማዳመጥ የሚባል ነገር አይታሰብም። ይህን አደጋ ፈጽሞ እንዲሁ በዋዛ ቸል ብለን
ልናልፈው አይገባንም።

እኔ በግሌ ከሰዎች ጋር ጉብረት ማድረግን በጣም የምወደው ነገር ነው። ብዙጊዜ
በጉብረት ከሰዎች ጋር እጸልያለሁ፤ እግዚአብሔርም በዚያ እንደሚባርከን እና እርስ
በእርሳችንም እንድንጠቃቀም እንደሚያደርገን አምናለሁ። የዚህ እውነታ ሌላኛው ገጽታ
ደግሞ ጉብረት ስናደርግ ሚዛን ጠብቀን መኖር እንዳለብን ነው። ብዙጊዜ በጸጥታ
ውስጥ ለብቻ መሆንን እናደርገውም።

ሁልጊዜ ሰዎች በዙሪያችን አሉ። ልጆች፣ የትዳር ጓደኛ፣ የመስሪያ ቤት ጓደኞች፣ ጎረቤት
ሥነራል። በመንገድ ላይ ስንሄድም ሰው አለ። ሌላ፣ ሌላም በዙሪያችን ሁልጊዜ
ልናስተናግዳቸው የሚገቡን እንቅስቃሴዎች አሉ። "እስኪ ቆይ እርሱ ይሂድና ይሆንን እና
ያንን እደርጋለሁ" እያልን ሁልጊዜ ሰው እያስተናገድን የምንኖርበት የባከነ የግርግር
ሕይወት ነው ያለን። እንዱን ነገር በጥድፊያ ሰርተን ስንጨርስ በዚያ ሥራ
እግዚአብሔርን ሳናመሰግንበት፣ እኛም የምስጋና ጊዜ በማዘጋጀት ደሰ ሳንሰኝበት ጸጥ
እንላለን። ከዚህ በኋላ የምሰራው ሥራ የለኝም እንዳንል ሌላው ይመጣል። አንዱን
ስንጨርስ ወደ ሌላው ፕሮጀክት መጣደፍ ነው። ይህንን አስተውሎ ይመስለኛል ኢዮብ
"የሰው ሕይወት በምድር ላይ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ አይደለም ወይ?" ያለው (ኢዮብ
7፥6)።

ስለ ሸማኔ መወርወሪያ የምታውቁ ይመስለኛል። የሸማኔ መወርወሪያ ምን
ዕረፍት አለው? ሸማኔው እንድ ጊዜ ሽመና ሥራው ላይ ቁጭ ካለ ተነሥቶ አስኪሄድ
ድረስ መውርወሪያውን ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ እጁ አየወረወረ ሲሠራ ነው
የሚውለው። ኢዮብ እረፍት እና ፀጥታ የሌለበትን በጥድፊያ የተሞላውን ይህን የሰውን
ልጅ ሕይወት አይቶ ነው በሸማኔ መወርወሪያ የመሰለው።

ብዙ ከርስቲያኖች ልባቸው ወደ እግዚአብሔር መጠጋት እየናፈቀ፣
ሕይወታቸው እግዚአብሔርን ለመምሰል እየተጠማ እያለ አረፍት እና ፀጥታ በማጣት
ምክንያት ግን የወከባ፣ የግርግር እና የጥድፊያ ኑሮ እየኖሩ ናቸው። እዲስ አበባ
ዩኒቨርስቲ በተመሳሳይ ማደሪያ ከፍል ውስጥ የነበሩ ከርስቲያኖች ሁልጊዜ ማለዳ ላይ
እየተነሱ ከአልጋቸው ይወርዱና ተንበርከክው ይጸልዩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ሁሉም
ተነሥተው መጸለይ እንደ ጀመሩ በእንቅልፍ ይተኃ የነበረው አንዱ ወንድማችን ግን
እንደ ተኛ ነበር። እነርሱም አልቀሰቀሱትምና ተኛ። እግዚአብሔር ረዳውና የሆነ ለዓት
ላይ ሲነቃ ሁሉም ሲጸልዩ ሰማ። ቀስ ብሎ ከአልጋው ተንሸራቶ ወርዶ አልጋው ሰር
በርከክ ብሎ "እኔም በሕይወቴ ብበረታ ምኞቴ ነው ጠዋት ማታ፤ የጥሞና ጊዜ አጣሁኝ"
የሚለውን መዝሙር መዘመር ጀመረ።

የእኛስ የሁላችን ሕይወት እንዲህ አይደለምን? እንደ ሸማኔው መወርወሪያ
ከአንዱ ወደ ሌላው ሽር፣ ሽው፣ ሽር፣ እያልን ዕረፍት የለንም። ሌላውን ተዉትና የጸሎት
ጊዜያችንን እንኳን ውሰዱት። ወደ ቤተ ክርስቲያን ብንመጣ የአምልኮ፣ ቃለ

አግዚአብሔር የሚሰበክበትን፣ የጸሎት እና ሌሎችም መንፈሳዊ ናቸው የምንላቸው እንቅስቃሴዎቻችንን ሁሉ እንኳን ካያቸሁት ሁሉም የየራሳቸው ድምፅ አላቸው፣ በአግዚአብሔር ፊት ጸጥ ብለን የምንቀመጥበት ጊዜ የለንም፡፡ እንዲያውም ጉባኤው ሞቅ ደመቅ ባለ ድምፅ የተሞላ ቀን "እቤት ዛሬ እምላክችን በዘርፋፋ ቀሚሱ በመካከላቸ ተመላለለ" ነው የምንለው፡፡ ድምፃችን ምድሩን ሰላናወጠው፣ ኮንፍረንሳችን ቅጥ አምባሩ በጠፋ ድምፅ ለለተሞላ ደለ ነው የሚለን፡፡

ለእኔ ግን መጽሐፍ ቅዱለ *"ሊያሱም ሕዝቡን፦ ለእ፦ ጩኹ አለከምልበት ቀ ድረስ አትጩኹ፣ ድምጻችሁን ሊታንሡ፣ ከአፋችሁም አንድ ቃል ላይወጣ፤ በዚያን ጊ ትጮኻላችሁ ብሎ አዘዘቸው" (ሊያሱ 6፣10)* አንደሚል ሊያሪኮን የሚያህል ትልቅ ግንብ እንኳን ለማፍረስ አግዚአብሔር ከአፋችሁ አንድ ቃል ላይወጣ ዝም በሉ እንዳላቸው ነው፡፡ አግዚአብሔር በፀጥታ ውስጥ የሚሰራም እምላክ ነው፡፡

ነቢዩ ኤልያስ ተሰፋ ቆርጦ እና ምርር ብሎት የአግዚአብሔርን ድምፅ ፈልጎ "ብሞት ይሻለኛል" ባለ ጊዜ አግዚአብሔር ወደ ኮሬብ ተራራ ወለዶ የተገለጠለት በፀጥታ ውስጥ እንጂ በእሳት እና በነጎድጓድ ድምጽ አልነበረም፡፡ ይህ ምን ይመስላቸኋል? ለካስ አግዚአብሔር የፀጥታንም ድምፅ ይወዳል፤ በፀጥታ ውስጥም መናገር ይችላል፡፡ በዚህ ዘመን እንደዚህ ዓይነት ልምምዶች ጠፍተዋል፡፡ እኔ ግን ሁልጊዜ የምመኘው ነገር ዘምረን፣ ጸልዮን፣ እሸብሸበን የሆነ ለዓት ላይ ሁላችንም ፀጥ ብለን የአግዚአብሔር የአምላካችንን ድምፅ መስማትን ነው፡፡ በጉባኤው መካከል ሦስት ወይም አራት ክቢያት ብንኖር የአግዚአብሔር መንፈለ ሰጦታዎች የሚገለጡ ቢሆንም ሁልጊዜ የፀጥታ ጊዜን ልንፈልግ ይገባናል፡፡

በነገሮቻችን መካከል ፀጥ ማለት እና ውለጣችንን ማዳመጥ ቀላል ነገር ባለመሆኑ በሂደት ይሄ ራሳችንን ልናለለምደው የሚገባ እንዱ ነገር ነው፡፡ ይህቺ ዓለም አንዲህ ዓይነቱን ነገር እንድናደርግ አትወድም፡፡ በዚህ ዓለም የሚሠራው ሁልጊዜ የጥድፊያ፣ የግርግር ድምፅ ነው፡፡ አንድ ጊዜ አንዱ ሰው ጓደኛውን "ለመሆኑ ሲታየኝ የምደብር ዓይነት ሰው አመስለለሁ ወይ? እውነቱን ንገረኝ፤ እንዳትዋሸኝ?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ጓደኛዬውም "ሂድና ለብቻው ሆነህ ራስህን አየው፡፡ ለብቻህ ምን ያህል ለዓት መቆየት እንደምትችል ካወቅህ ያንጊዜ ራስህን ታውቀዋለህ" ሲል መለለለት፡፡ ለውየው ብቻውን መሆን ካልቻለ፥ ለደቂቃ መቆየት ምርር ብሎት የሚመጣ ከሆነ

ለሌላውም ለው እንደዚያው ነው ማለት ነው፡፡

ለብቻ መሆን፣ ፀጥታ፣ እርጋታ ምንድነው? ፀጥ ማለት ለተወለነ ጊዜ ያህል ወሬን እና ፈቅደን ከንግግር ወይም ከሥራ እንቅለቃሴ በመቆጠብ በመንፈሳዊ ሕያዉታችን ላይ ትኩረት ማድረግን መለማመድ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ጸም ለተወለነ ጊዜ ከምግብ የምንከለከልበት ነው፡፡ ከምግብ የምንከለከልበትም ምክንያት አለን፡፡ ያለ ምክንያት ዝም ብለን ሥጋችንን ምግብ ከከለከልነው የረሃብ አድማ ነው ሞጊሆነው፡፡ ለለዚህ ለንጸም ምክንያት ሊኖረን ይገባል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ወደ አግዚአብሔር ለመጠጋት የአግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግ መሆን አለበት፡፡ አናም ጸም ወደ አግዚአብሔር ለመጠጋት ፈቅደን ለተወሰነ ጊዜ ከምግብ የምንከለከልበት ነገር ነው፡፡ በአግዚአብሔር ፊት በዝምታ እና በፀጥታ ተረጋግተን የምንቀመጠው መጽሐፍ ቅዱለ ለማንበብ፣ ቃሉን ለማለላለል፣ ለመጸለይ፣ መንገዳችንን በአግዚአብሔር ፊት ለማሄድረግ ራሳችንን ለማየት የምንወሰደው የፀጥታ ጊዜ ነው፡፡

ይህን የምናደርግ ከሆንን በዙሪያችን የሚለማውን የድምፅ ሞገድ ነውጥ በፈቃዳችን አምቢተኝነት ላለማዳመጥ ፀጥ አሰኝተን፣ በየሕይወት እውዱ አናታችን ላይ ቁበ ብሎ የከተመውን ጉባኤ ከበተንን፣ ራሳችንን ለፀጥታ እና ለብቻ በእርምጭ የሠቀመጥ ሥርዓት ለማለገዛት በቅተናል ማለት ነው፡፡ እየሩ ላይ እየተመመ ከሚፈለው ከሰው ጫጫታ እና ሁካታ ርቆ እና ተነጥሎ ከሰው ተሰርቆ ለብቻ መሆን መቻል ትልቅ የሕይወት መርህ ነው፡፡ እንዲህ መሆን ደግሞ ቁርጠኛ ውሳኔን ይፈልጋል፡፡ ከአግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን የሁለትዮሽ ግንኙነት ነፍስ እና ሥጋን በዚህ መልኅቅ ላይ እስቀምጠን ጋብ ረገብ የምንልበት መርህ ፍኖቱ ይህ ነው፡፡ በቃ! ከአግዚአብሔር ጋር በፀጥታ መሆን፡፡

ብላቴናው ሳሙኤል አግዚአብሔር "ሳሙኤል" ብሎ በለሙ በጠራው ጊዜ ሳሙኤል "እቤት" ብሎ የሄደው ወደ ኤሊ፤ ወደ ሰው ነበር፡፡ ምክንያቱም ልምምዱ ወደ ኤሊ. መሄድ ብቻ ለለነበርና የሚያውቀው ኤሊን ለለነበረ ነው፡፡ ለብቻ ሳሉ በለም የሚጠራ እምላክ መኖሩን ገና አልተለማመደም ነበርና፡፡ ኤሊም ለሳሙኤል እንዲህ ሲል ነገረው "ከጠራህ ብቻህን ለለሆንክለት ነው የጠራህና አቤት፤ ባሪያህ ይሰማሃል በለው" አለው፡፡ ጸጥታ ፈቅደን ከሌላው ግርግር ወጥተን ለጊዜው ለብቻችን በመሆን ዝም እንድንል "አምን ብቻዬን መሆን አፈልጋለሁ" በሚል ጽኑ ውሳኔ ልንታጠር ይገባል፡፡

አያችሁ ለብቻ መሆን ሊቃይ የሚሆነው ብቸኝነቱ በሽታ ሲሆን ነው፣ በእግዚአብሔር ፊት ለብቻችን ስንሆን ግን እግዚአብሔርን የምናይበት፣ ለንስሃ ለምስጋና፣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ፣ ለሙታን የምንችልበት መንገድ ይሆናል፣ ይሄ ቀላል ልምምድ ባይሆንም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መሆን ያለበት ነገር ነው።

አንከር ዳንከራተር የተባለው የአሜሪካው ሲ. ቢ. ኤስ. ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ አንድ ወቅት ላይ ማዘር ተሬዛን ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር። ዳንከራተር በዚህ ቃለ መጠይቁ ከማዘር ተሬዛ ማወቅ የፈለገው አንድ ነገር ብቻ ነበር። ያም እግዚአብሔር አንዴት አንደሚናገራቸው ማወቅ። ለለዚህም ቢደረገላቸው ቃለ መጠይቅ "ለመሆነ አርለም ሲጸልዩ ምን ብለው ነው የሚጸልዩት? እግዚአብሔርንስ ምን ብለው ነወ የሚያናግሩት?" ሲል ጠየቃቸው። ማዘር ተሬዛም ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ "ምንም አልለውም፤ ነገር ግን እርሱ የሚለኝን ነው የምሰማው" አሉት።

ይህ ጋዜጠኛም ጥያቄዬን በደንብ አልተረዱኝም ብሎ አሰበ መልሶ "ማለቴ ሲጸልዩ እግዚአብሔርን ምን እና እንዴት ብለው ነው የሚጠይቁት?" አላቸው። እርሳቸውም መልሰው "ምንም አልለውም፤ ብቻ የሚለኝን ነው የምሰማው" ነበር ያሉት። ጋዜጠኛው አሁንም ጥያቄውን እንደገና ዘወር አድርጎ "ታዲያ እርሱ የሚሰማዎት ከሆነ እርስዎ ምን ይሉታል?" አላቸው። ማዘር ተሬዛም "ምንም አልለውም፤ ግን ይሰማኛል።" ይሆን ጊዜ ጋዜጠኛው ግራ ተጋብቶ ዓይኑን አፍጥጦ ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው ማዘር ተሬዛም ዓይን ዓይኑን እያዩት "የምልህ ካልገባህ ይቅርታ፤ እኔም ከዚህ በላይ ላስረዳህ አልችልም" አሉት። በጣም የሚገርም መልስ፤ ደግሞም የሚገርም ልምምድ ነው።

አዎን፣ በእግዚአብሔር ፊት ልብን እና አዕምሮን ከፍቶ ነገርን አረጋግቶ ዝም እና ፀጥ ብቻ የማለት ሕይወት አለ። ሁልጊዜ ድምፅ፣ ግርግር፣ እና ጥድፊያ ከበዛባት ዓለም በመውጣት ለእግዚአብሔር መገኘት እና ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ መውሰድ ይኖርብናል። "ከዓለም ወጥተን ለብቻችን እንሁን" ስል ጉዳም አንግባ ማለቴ አይደለም። መንፈሳዊ ነገር የውስጥ ሰውነታችን ልምምድ ጉዳይ እንጂ ጉዳም በመግባት የምናመጣው ነገር አይደለም።

ስለ ጉዳም ሳስብ ሁሌ ትዝ የሚለኝ አንድ ታሪክ አለ። ሦስት ጓደኛሞች ተያይዘው ጉዳም ገቡ አሉ። እናም አንድ ቀን አነዚህ ጓደኛሞች በቃ ዛሬ አንነጋገርም ተባባሉ። የተወሰነ ሰዓት ያህል በዝምታ ከቆዩ በኋላ አንደኛው እንዲህ አለ።

"እናንተ፣ ዝም ብሎ መዋል እንዴት ከባድ ነው አባካችሁ!" አላቸው። ይኼኔ ሁለተኛው ቀጠለና "እንተ ምን ማለትህ ነው፤ አንነጋገር አልተባባልንምን? አሁን እኮ አሦናገርክ ነው" አለው። የሁለቱን ጓደኞቹን ንግግር የሰማው ሦስተኛውም "እስካሁን ያልተናገርኩት እኔ ብቻ ነኝ" አላቸው።

ዝም እና ፀጥ ብሎ መቆየት ልምምድ በመሆኑ ቁርጠኝነትን፣ የግል ውሳኔን እና ለውሳኔው መሰጠትን ይጠይቃል። እምን አሁን ሳይሳካልኝ ቀርቶ ልወድቅ እችል ይሆናል፤ ሆኖም ደግሜ ደጋግሜ በመለማመድ እንደሚደርገው ግን ጥርጥር የለውም።

መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር 131፣2 ላይ ሲናገር አንዲህ ይላል። *"ነፍሴን ለሳረፍኋት፣ የእናቱንም ጡት ለጓጎለቱት ዝም አለንኋት፤ ነፍሴ የእናቱን ጡት ለጓጎለቱት በለኔ ውስጥ ናት"።*

ይሆንን ጥቅስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ *"ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም ለሰኝኋት"* ነው የሚለው። ዳዊት ስለ ምን ዓይነት የአረፍት እና የዝምታ ሕይወት ነው የሚያወራው? ጡት የጣለ ህጻን ከሌላው ተለይቶ እናቱ ላይ አርፎ የተቀመጠ ወደ እናቱ የሚጠጋ ነው። ለእርሱ እናቱ አለምሮው፣ ፍላጎቱ ናት። ያ ህጻን ዓይኑም፣ ልቡም ያለው እንድ ስው ላይ ሲሆን፤ እርሷም እናቱ ናት። "ነፍሴ ትኩረቷን እግዚአብሔር ላይ አድርጋ እርሱን ብቻ እንድትፈልግ፣ አንድትሻው ዝም፣ ጸጥ፣ አርፍ እንድትል አደርግኋት" ማለቱ ነው ዳዊት። ይሄ እንዴት ያለ ልምምድ፣ እንዴት ያለ ሕይወት ነው? ጉዳም ገብተን ሳይሆን፤ በዓለም ውስጥ እየኖርን፣ መስሪያ ቤት ሄደን እየሠራን፣ ትዳር ውስጥ ሆነን፣ ተማሪዎች ሆነን፣ ባልንጀሮች እያሉን፣ ከጓደኞቻችን ጋር ሆነን ቤተ ክርስቲያን እየሄድን፣ አገልግሎት እያገለገልን፣ ጎብረት እያደረግን ዝም፣ ፀጥ በማለት ለእግዚአብሔር ብቻ የምንገኝበት የብቸኝነት ጊዜ አለ ማለት ነው።

ለብቻችን በፀጥታ መቀመጥን መለማመድ ለምን እንደሚጠቅም የምናየው የኢየሱስን የሕይወት ምሳሌዎች በመውሰድ በመሆኑ፤ እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ልምምዶች ስንነጋገር የኢየሱስን የሕይወት ምሳሌነት እያነሳን በየተራ የምናይ ይሆናል።

የተጠራነው እርሱ ያደረጋቸውን ነገሮች እናደርግ ዘንድ ነው።

ጌታ እገልግሎቱን እንዴት እንደ ጀመረ ማቴዎስ በወንጌሉ ሲነግረን *"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው"* (ማቴዎስ 4፥1) ይለናል። በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ በርግብ እምሳል በላዩ ላይ ሲወርድ፣ አብ ከሰማይ *"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይሄ ነው፤ እርሱን ስሙት"* ካለ በኋላ በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። ከዚያም እገልግሎት የሚጀምርበት፣ የሚገለጥበት ጊዜ ስለመጣ አርባ ቀን ሙሉ ለብቻው በጸጥታና በእረፍት ቆየ። ሰምን? የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ እና ትዕዛዙን ለመፈጸም ራሱን የሚሰጥበት ጊዜ ስለሆነ።

ከዚያም እግዚአብሔር ለሰጠው ተልዕኮ የሚገለጥበት ሰዓቱ ስለ ደረሰ ቀንም ሌሊትም ዝም፣ ጸጥ የሚልበት በእግዚአብሔር ፊት ለእግዚአብሔር ብቻ ተለይቶ የሚሆንበት ጊዜ ሆነ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የብዙዎቹን የእግዚአብሔርን ሰዎች ሕይወት ተመልከቱ፤ በደንብም መርምሩ። በኢየሱስ ከርስቶስ ሕይወት የምናያቸውን ነገሮች በብዙዎቹ አገልጋዮች ሕይወትም ውስጥ ማግኘት ትችላላችሁ። እያንዳንዳቸውን እግዚአብሔር የጠራቸው፣ ራእይን የተቀበሉት እና መንገዱን ያሳያቸው ብቻቸውን በእግዚአብሔር ፊት ዝም፣ ፀጥ ብለው በተቀመጡበት ጊዜ ነበር።

ማነው ከእኛ መካከል ምስጢሩን እየሮጠ ላለ ለሌላው ለው የሚናገር? በእኛ ዘንድ ምስጢሩን ሁሌ ለሚያባክን፣ መቆሚያ ለሌለው፣ እጁ፣ እግሩ፣ አፉ፣ ሁሉ ነገሩ በሩጫ፣ በጥድፊያ ለሚኖር ለው የሚናገር ማን ነው? አንግዲያው እኛ እንዲህ የማናደርግ ከሆነ ሰማይ እና ምድርን የሰራ የእኛ ጌታማ እንዴት በፊቱ ፀጥ ብለው የሚቀመጡትን፣ ውሰጣቸውን ዝም ያሰኙትን ሰዎች እንዴት አብልጦ አይሻ! ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ እና ዝግ ብሎ የጥሞና ጊዜ መውሰድ ለእገልግሎት ዝግጅት ቦታም እስፈላጊ ነው ማለት ነው።

ሉቃስ በወንጌሉ *"በእነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ"* (ሉቃስ 6፥12) ይለናል። *"በእነዚህም ወራት"* የሚለው ቃል በወራት ለሚቆጠሩ ተከታታይ ቀናት መቆየቱን ነው የሚያመለክተን። ጌታ ኢየሱስ ሰዎችን ይፈውስ፣ ይሰብክ እና ያስተምር የነበረበትን አገልግሎቱን አቋርጦ ለብቻው ወደ ተራራ የወጣው በአምላኩ እና በአባቱ ፊት ፀጥ

ሞሊልበት የጥሞና ጊዜ ለመውሰድ ነበር። የአባቱ ፈቃድ ምን እንደሆነ እጥርቶ ያወቀው የፀጥታ እና የጥሞና ጊዜ ከወሰደ በኋላ ነው። እግዚአብሔር የሰጠው ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አነ ማን እንደሆኑ ለይቶ በማወቅ የመረጣቸው እና ሐዋርያት ብሎ የሾማቸው ከዚያ በኋላ ነው። ከምን በኋላ? በአባቱ ፊት ከፀጥታ፣ ከዝምታ እና ከጥሞና ጊዜ ቆይታ በኋላ።

ወገኖቼ ሆይ! ብዙጊዜ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በሕይወታችን ለማወቅ ሞጂዮዳግተን እግዚአብሔር ፈቃዱን ከእኛ ደብቆብን፣ መንገዱን ሰውሮብን፣ ዱካውን እጥፍቶብን አይደለም። ዳዊት "በአኔ መሞት ምን ጥቅም አለ"? ብሎ ወደ እግዚአብሔር እንደ ጮኸው። እግዚአብሔር ፈቃዱን ከእኛ ቢሰውርብን ምን ይጠቀማል? ወገኖቼ ሆይ! እግዚአብሔር ፈቃዱን ከሕዝቡ የሰወረበት ወቅት የለም። ይሁንና ፈቃዱን ልንሰማ፣ ልንረዳ እና ልንፈጽመው የምንችለው ግን ከውጥንቅጥ ነገሮች መካከል ወጥተን ለብቻችን በእርሱ ፊት በዝምታ፣ በጸጥታ መሆንን ስንለማመድ ነው።

ሌላ አንድ ነገር ልጨምር። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ አንድ ጊዜ ሰዎች መጥተው ለጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ "መጥምቁ ዮሐንስ ታሰረ" አሉት። እርሱም ሙታሰሩን ሲሰማ ወደ ገሊላ ፈቀቅ ብሎ ሄደ። ቆየት ብሎ ደግሞ "እንጉቱን በሰይፍ ቆርጠው ገደሉት" ብለው ሲነግሩት፣ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ ቢታንኳ ፈቀቅ አለ።

ወንጌላውያኑ በጣም ታማኝ ጸሐፊያን ናቸው። ሲጽፉ ነፍሰ ገዳዩ ሲነሳ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማጥፋት እና ለማበላሸት የሚሹ ኢጋንንት ሲራኮቱ፣ ጌታ "ከፊታቸው ፈቀቅ፣ ዘወር፣ ፀጥ፣ ዝም አለ" በማለት እጸፋውን እንደ መለሰላቸው ነው በታማኝነት የዘገቡልን። ጌታ ኮንፍረንስ በማድረግ አጸፋውን አልመለሰም። በሕይወቱ ተግባራዊ ያደረገው ጥበብ እንዲህ ዓይነቱን ነው።

ጌታ መቼ መናገር እንዳለበት ሰለሚያውቅ፤ ሲናገርም እጥርቶ ይናገር ነበር። ሲያሰኘው ደግሞ በድፍረት ቁጥኛ በሆነ አነጋገር "ለዚያች ቀበሮ እንዲህ በሏት" የሚልበት ጊዜ ነበር፤ ዘወር የሚልበት ጊዜም ነበረው። እግዚአብሔር ሁላችንንም በዚህ ጥበቡ ይሙላን። ጌታ አልፎ በመሰጠት መከራን የሚቀበልበት ሰዓት እንደ ደረሰ ባወቀ ጊዜ ምን እንዳደረገ ሁላችንም እንዘነጋውም ብዬ እምናለሁ። ታስታውሱ እንደሆነ ግርግሩን ተውት በማድረግ ወደ እትክልቱ ስፍራ ነበር ፈቀቅ ያለው። ነገሩ ለብቻ የመሆን፣ የፀጥታ ጊዜ የመውሰድ ጉዳይ ሰለነበር ሦስቱን ደቀ መዛሙርቱን እዚህ ቆዩኝ

ብሎ የድንጋይ ውርወራ ያህል ትቷቸው ከአነርሱ ፈቀቅ ብሎ በመራቅ ከአባቱ ጋ በፀጥታ መነጋገር ጀመረ።

ወገኖቼ ሆይ! በሕይወታችን "ጌታ ሆይ ቢቻልህስ ይሄ ከእኔ ይለፍ" በምንለዉ ብርቱ ለልፍ ወይም ከባድ የመከራ ወጀብ ውስጥ ልናልፍ እንችላለን። በአጣብቂኝ ውስጥ ጉብተን ነፍሳችን "ህቅ!" ብላ ልትወጣ ልንደርስ እንችላለን። ለዚህ መፍትሄዉ መሮጥ፣ መሸሽ ወይም መባከን አሊያም የፈተናዎቻችንን ከብደት እና መራርነት እያወራ መዘር ሳይሆን፤ መድሃኒቱ ብቻችንን በአግዚአብሔር ፊት መቀመጥ ነው። በዚያ ጌታ እንዴት ለልባችን እንደሚናገረን፣ እንደሚያጽናናን፣ ፈቃዱን እና ሐሳቡን በነፍሳችን ውስጥ እንደምን እያንቆረቆረ እንደሚያስቀምጥ ያውቅበታል።

በእርሱ ፊት ዝም እና ፀጥ ብለን በአግሮቹ ስር እርፈን ስንቀመጥ፤ አግዚአብሔር አምላክ መሆኑን አውቀን ጣጣችንን እዚያው ጨርሰን እንነሳለን። ያን ጊዜ "እረፉ፤ እኔም አምላክ እንደሆንኩ እወቁ" የሚለው ቃሉ በሕይወታችን አውን ይሆናል።

ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ ዝም፣ ፀጥ እና ፈቀቅ ብሎ የሚሄደው ለእገልግሎቱ እንደገና ኃይል መሞላት እና መታደስ እንዲሁም ለሌላ እገልግሎት መዘጋጀት ሲፈልግ ነው። *"ጻሕይም ጦበቶ በመሸ ጊዜ . . .በልዩ ልዩ ደዌ ይታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፣ ብዙዎችንም ሊጋንን አወጣ . . .ማለዳም ተነሱቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ፤ ወደ ምድረ በዳም ሄደ በዚያ ጸለየ" (ማርቆስ ፡፣32-36)* ይለናል። ወደ ምድረ በዳ የሄደበት ያ ሰዓት ፀጥ የሚልበት፣ ከአባቱ ጋር የሚነጋገርበት ሰዓት በመሆኑ ነው።

ከአባቱ ጋር የተነጋገረው በቀጣይ ከፊቱ ለሚጠብቀው ሥራ እንደገና ኃይሉን ማደስ ይችል ዘንድ ነው። ወንጌላዊው ሉቃስም *"ወፈው ግን አብዝቶ ወጣ፤ ብዙ ህዝብም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰባሰቡ ነበር፤ ነገር ግን አርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር" (ሉቃስ 5፡15)* ብሎ ይነግረናል። አይገርምም፧ ወፈው ወጣ፤ ዝናው በዙሪያው ባሉ ከተሞች ሁሉ ናኘ። ስለዚህም ብዙ ህዝብ ሊሰሙት፣ ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር።

ሌላኛው ወንጌል ጸሐፊ ደግሞ *"፡ . .ለየመጡ ፈውሰ ፍሊጋ በላዩ ላይ ይወድቁበት ነበር"* ብሎ ይነግረናል። እንዲህ ባለ ለዎች በብርቱ እየቃተቱ አርሱን በሚፈልጉበት ሰዓት ላይ አርሱ ግን ዘወር ብሎ ወደ ምድረ በዳ ነበር የሚሄደው። አቤት

እነሄሉት ያለ ታላቅ የሕይወት ምስጢር ነው! ጌታ ኃይላችንን የምናድስበት መንገድ ይህ እንደሆነ ስለሚያውቅ እና በራሱም ሕይወት የተለማመደው ይህንኑ ለልሆነ ለደቀ መዛሙርቱ *"እናንት ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት አረፉ" (ማርቆስ ፡፣)* አላቸው። የሚመጡና የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና ከሥራው ብዛት የተነሳ ያን ያህል ባተሌ ሆነው ለመብላት እንኳን ጊዜ አጥተው በነበረበት ሰዓት ጌታ "አቁሙ! አሁን ምዝምታ ጊዜ ያስፈልጋል" አላቸው።

በዮሐንስ ወንጌል ላይ ሁላችንም የምናውቀው አንድ ታሪክ አለ። ጌታ ለተራበው ህዝብ እንጀራውን እና ዓሣውን አትረፍርፎ ሲሰጣቸው ህዝቡ በጣም ደስ ብሏቸው ለነፍሳችንም ሆነ ለሥጋችን የሚሆን ምግብ የሰጠን *"ይህ በለውነት ወደ ዓለም ሥሃመጣው ነቢይ ነው አሉ። በዚህም ምክንያት ሊየሱስ ሊያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ለነነሣት እንዳላቸው አውቆ ወደ ተራራው ብቻውን ፈቀቅ አለ" (ዮሐንስ 6:8-15)* ብሎ ይነግረናል። "እንዲህ ያለውን ድንቅ አገልጋይማ እንዴት እንለቀዋለን!? የትም መሄድ የለበትም፤ እንፈልገዋለን" ነው ነገሩ። እኔ፣ አንተ እና አንቺ፣ እኛ ብንሆን ግን ይህን የመሰለ ተዓምራት ካደረግን በኋላ እገር ቢፈልጉን ያጣናል እንዴ? አያጣንም! ለምን? ምክንያቱም ወደ የትም ዘወር፣ ፈቀቅ አንልም። እዚያው ግርግሩ፣ ትርምሱ፣ የሁካታው ድምፅ ውስጥ ነው የምንቆየው። እንዲያውም አንደ ባንዲራ ከፍ ብለን ለሁሉ ሰው ለመታየት ባንፈልግ ነው!? ጌታ ግን ሊያደርጉ ያሰቡትን ያውቅ ለለነበር ፈቀቅ በሚባልበት ለዓት ወደማይገኝበት ስፍራ ዘወር አለባቸው።

ከዚያም ዮሐንስ ሊናገር ምን ይላል *"በነጋውም ከባሀር ማዶ ቆመው የነበሩ ህዝብ ከለንዲት ጀልባ በቀር በዚያ ሌላ ጀልባ ለንዳልነበረች፣ ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው እንደሄዱ ለንጂ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ ለንዳልገባ ለዩ፤ ሕዝቡም ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ ለንዳልነበረ ባዩ ጊዜ ራሳቸው በጀልባዎቹ ገብተው ኢየሱስን ለየፈለጉ ወደ ቅፍርናሆም መጡ። በባሀር ማዶ ሊያገኙት፡- መምህር ሆይ ወደዚህ መቼ መጣህ? አሉት። ኢየሱስም መልሶ፡- ለውነት፣ ለውነት ለላችኋለሁ የምትፈልጉኝ ለንጀራን ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ ለንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ ለይደለም ለላቸው" (ቁጥር 22,24)* ይለናል።

እነዚህ ሰዎች ፈቀቅ የሚባልበት ሕይወት፣ በአግዚአብሔር እምላክ ፊት ለብቻ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ አልተረዱም። ወገኖቼ ሆይ እኛስ? የዚህን ዘመን ኑሯችንን

አይተን ምንድነው የምናስበው? ቅድም እንዳልኳችሁ ጥድፊያ፣ ግርግር እና ትርምሳ ያለበት ሕይወት ውስጥ መኖር አልሰለቻችሁምን? አሰኪ አንድ ቀን ብድግ በሉና ብቻችሁን ሳሎን ቤት ማለዳ፣ ወይም ማታ ልጆች ከተኙ ወይም አብሮ የሚኖር ሰው ካረፈ በኋላ ዝም ብላችሁ ውጪ ወጥታችሁ ሰብቻችሁ ቁጭ በሉ። ቤት ውስጥ ወይም ሥራ ቦታችሁ ላይ ጊዜ ካገኛችሁ ለብቻችሁ አንድ ቦታ እልፍ ብላችሁ ተሰወሩና ሞክሩት። ያገኛችሁ ሰው በሙሉ "ምነው በደህና፣ በሰላም ነው?" ነው የሚላችሁ። ምክንያቱም አልተለመደማ! ሁላችንም ያለነው በትርምሱ፣ በሁካታው ውስጥ በመሆኑ አሁን ከዚያ ውስጥ መውጣት ይኖርብናል። አግዚአብሔር ዝም፣ ፀጥ፣ እርፍ የምንልበትን ሕይወት ይስጠን!! ይሆንን ሕይወት ሰመለማመድ ምንድነው ማድረግ ያለብን?

ቀደም ብሰን አንደ ተነጋገርነው ይህ ትውልድ ፀጥ ብሎ ለብቻ መሆንን የሚፈራ ሆኗል። ትውልዱ ብቻውን መሆንን ስለፈራ ተከቧል። በኮምፒዩተሩ፣ በታብሌቱ፣ በስልኩ፣ በቴሌቪዥኑ፣ በሬዲዮው፣ ምኑ ቅጡ! ከፉኛ ተከቧል። አግዚአብሔር በሥርዓት በተመራ ሕይወት ይህንን እና ሌላውን ሁሉ አቋርጠን "እምቢኝ" የሚባለውን ሁሉ "እምቢ!!" ብለን፣ የሚዘጋውን ጥርቅም አድርገን ዘግተን በፊቱ ፀጥ ብለን ሕይወታችንን፣ መንገዳችንን ስናይ፣ ስንመረምር ማየት ይፈልጋል።

አህቶች አብረው አየተጫወቱ አያሉ ከመካከላቸው አንዲ አንዳች ቃል ሳትናገር የሚነጋገሩትን ዝም ብላ ታዳምጣቸዋለች። አናም ሁኔታዋን የተመለከተቻት አንዲ "አንቺ ቆርበሻል አንዴ ለምንድነው የማትናገሪው?" አሰቻት። ለነገሩ አኩርፋም ሊሆን ይችላል። እኔ ያንን ዓይነት ዝምታ ዝም አንበል አያልኩ አይደለም። ነፍሳችን ዝም የምትልበት ትክክለኛ ጊዜ ያስፈልጋታል።ዝም፣ ጸጥ ማለት ከአግዚአብሔር ጋር ያሰን ጉዳይ ለመንፈሳዊ ሕይወት ትኩረት ለማድረግ የምናደርገው ነው ማለት ነው። መነኩሴ የሚለው ቃል "ሞነኮ" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፤ ትርጉሙም መነኩሴ ማለት ነው። ስለዚህ ሳናውቀው እንደ ግሪክ ያደርገናል ማለት ነው።

ሞነኮ የሚለው ቃል ትርጉሙ ያልተከፋፈለ፣ አንድ ብቻ መሆን ማለት ነው። እና እኔ ሳልከፋፈል የጌታ ብቻ የሚያረገኝ ከሆነ መመንኮስ ይብዛብኝ እንዴ? በሕይወታችን የሚያስፈልገን ምንድነው? አግዚአብሔርን ባልተከፋፈለ ልብ፣ አእምሮ እና ሐሳብ መወደድ፣ ማሰብ አይደል እንዴ?

አንዳንድ ጊዜ መመንኮስ ሲያስፈልገን በዚህ መንገድ አናድርገው። አንደኛ የምናወራው ነገር ልምምድ ሰሰሆነ ልምምዱ ቦታ እና ጊዜ ስሰሚያስፈልገው ቦታ እና ጊዜ እንወስንለት። "ይሄንን በዚህ ቦታ እና በዚህ ሰዓት እደርገዋለሁ" ብላችሁ የምትወስኑት እና የምታደርጉት ነገር መሆን አለበት። ይሁንና በሰማነው የአግዚአብሔር ቃል ልባችን ሲነካ ተነስተን ለራሳችን "ከዛሬ ጀምሮ ቁርጥህን አውቅ፤ ሌሊት ስምንት ሰዓት ከመኝታ ትነሳለህ። እሰከ አሰር ሰዓት ድረሰ. . ." የሚል ዘለቄታ የሌለው የድፍረት ውሳኔ አንድትወስኑ አልፈልግም። በትንሹም ቢሆን በየዕለቱ ሳናቋርጥ የምናደርገው ነገር መሆን ነው ያለበት።

አግዚአብሔር ነገሮችን ያለ ማሰለስ አተኩሮ በጥብቅ የሚያይ አምላክ በመሆኑ ውሳኔያችንን አክብረን መቆማችንን ይመለከታል።

አንድ ታሪክ አንብቤለሁ። ስውዬው ሁልጊዜ ወደ ሥራው ሲሄድ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ቆም ይልና ጸሎት ያደርጋል። እና ልጁም አብሮት ይቆማል። ሰውዬው ዝም ብሎ ይቆምና "ኢየሱሰ ሆይ በዚህ አሰሁኝ" ብሎ ይሄዳል። አናም ሁልጊዜ "ኢየሱሰ ሆይ በዚህ አሰሁኝ" ብሎ ነው የሚያልፈው።

ከዕለታት አንድ ቀን ግን ያንን ጸሎቱን የሚጸልይበት ሰዓት ከመድረሱ በፊት መንገድ ላይ የመኪና አደጋ ይደርሰበትና ሆሰፒታል ድንገተኛ ከፍል ይገባል። ሰውዬው ነቅቶ ዓይኑን ሲገልጥ ድንገተኛ ከፍል ውስጥ ያሉ ሐኪሞችን ግርግር ይመለከታል። ጊታም ያችን የጸሎት ሰዓት አከብሮ አጠገቡ ቆሞ "ልጄ እኔ ኢየሱሰ ነኝ፤ በሰዓቱ ተገኝቻለሁ" አሰው።

ጌታ ግንኙነቶቻችንን ያክብራል። ጊዜ፣ ቦታ፣ ለይተን አክብረን ከእርሱ ጋር የምንሆንበት የብቻ ጊዜ ሰናደርግ እርሱ ቀጠሮ የማይሰጥ ታማኝ ነው። ጥቂትም ይሁን እንዲህ ጊዜ እና ቦታ ለይተን ልናደርግ የተነሳንበት ጊዜያችንን በጸሎት ጀምረን በጸሎት መጨረስ አለብን። ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድ ጸሎት ስለሆነ፤ በወቅቱ መሉ ትኩረታችን ጸሎት ላይ ስለሚሆን እንደዚህ በምናደርግበት ጊዜ ወጥ ዝም በማሰት ከሌላው ሁኔታ ተለይተን በእግዚአብሔር ፊት በመሆን አግዚአብሔርን ብቻ ማሰብ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ እናደርጋለን እንልና ወዲያው ግን ወደ አእምሯችን እንደ እቁብ፣ እድር የመሳሰሉ ሐሳቦች የሚመጡብን ከሆነ፤ የፀጥታ ጊዜያችን ተደናቀፈ ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል "ፈጣሪህን አስብ" ስለሚለን እግዚአብሔርን አስቡ፡ መንገዱን ፈልጉ፣ በእርሱ ደስ ይበላቸሁ፤ ምህረት ባደረገልን አስትንፋስን በውስጣችን ባስቀመጠው አሁንም ሆነ ወደፊት ወደ እርሱ የምንቀርብበትን በር በከፈተልን ሁልጊዜ ወደ እርሱ እንድንመጣ በሚፈቅድ ጌታ ደስ ይበለን።

ወገኖቼ ሆይ አመሰግኑ። አእምሯችንንም ሆነ ሐሳባችንን ሰጥተን "ማድረግ የምንፈልገው ነገር ይሄንን ነው" ማለት ስንጀምር፤ ያንጊዜ በለውነታችን፣ በአእምሯችን፣ እና በነፍሳችን ልምምድ እያደረግን ነው። በኋላም ዳዊት "ነፍሴ የአናቱን ጡት እንዳስተውት ህጻን በውስጤ ዝም፣ ጸጥ አለች" እንዳለው፤ ነፍሳችን ዝም ትላለች። ኢየሱስ ይሄን ካደረገ አርሱ ያደረገውን ሁሌ ብናደርገው፤ ዛሬ ተሳክቶልን ነገ እምቢ ቢለን አንኳን ተስፋ ሳንቆርጥ ተመልለን ያንኑ ደግመን ደጋግመን ብንለማመደው ኢየሱስን ወደ መምሰል እንደርሳለን። እርሱ ያደረገውን ማድረግ አርሱን ወደ መምሰል ያደርሰናል።